# ጠ

**ጠ** ከ"ገ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል(ግእዙ ሆሄ)።

**ጠሀነነ** ግ ጀነነ፥ አኮራ።

**ተጠሀነነ** ግ ተጀነነ፥ ኮራ።

**ጠሆኘ**[1] ግ 1. ተናደደ፥ ተቆጣ፥ ተበሳጨ። 2. መታ፥ ጠለዘ፥ መደወተ።

**ጠሆኘ**[2] ግ ፈጨ፥ አደቀቀ።

**ጠለለ** ግ 1. ጠራ፥ ኩልል አለ፥ ዝቃጩ ወደታች የተጣራው ወደላይ ሆነ። 2. ተጣራ፥ ነጠረ(ወርቅ፥ ብር፥...)።

**ጠለላ** ስ የጠለለ አጓት።

**ጥላይ** ቅ የጠለለ፥ የተጣራ (ፈሳሽ) ።

**አጠለለ** ግ 1. አጣራ፥ አቀረረ። 2. አተላው ወደታች ዘቅጦ የተጣራው ወደላይ ሆነ።

**ማጥለያ** ስ ከሸቦ ወይም ከስንደዶ ተታቶ የሚሰራና ለማጥሪያነት ወይም ለማጥለያነት የሚያገለግል ወንፊት መሰል እቃ፤ ወንጠፍት።

***ጠለለ**[1]

**ተንጣለለ** ግ 1. በብዛት ፈሰሰ፥ ተኛ፥ ተጥለቀለቀ (ውሃ፥ ደም፥...)። 2. ሰፊ ሆኖ ተሰራ (ቤት፥ ድንኳን፥...)።

**አንጣለለ** ግ በስፋት ሰራ፥ ተከለ (ቤትን፥ ድንኳንን፥...)።

***ጠለለ**[2]

**ጠለላ** ስ ከለላ፥ ተገን።

**ተጠለለ** ግ ተከለለ ወይም ዳነ (ከዝናብ፥ ከፀሃይ፥ ...)።

**መጠለያ** ስ 1. መከላከያ (ከዝናብ፥ ከፀሃይ፥ ...)። 2. መጠጊያ፥ ማደሪያ፥ ማረፊያ ቦታ።

**አስጠለለ** ግ 1. አስጠጋ፥ ለጊዜው ማረፊያ ወይም ማደሪያ ሰጠ። 2. መጠለያ ወይም ተገን ሆነ። *ዛፉ አያስጠልልም።*

**ጠለላ**[1] "**ጠለለ**" ስር ተመ.

**ጠለላ**[2] "***ጠለለ**[2]" ስር ተመ.

**ጠለመ** ግ ውሃ ውስጥ ሰጠመ፥ ዘቀጠ። 2. ጠፋ፥ ጠልቆ ቀረ።

**ጠለሰ** ግ ጥላ ጣለ፥ ጠለስ ሆነ።

**ጠለስ** ስ የፀሃይ ብርሃን በቀጥታ የማያገኘው ወይም የማያርፍበት ቦታ ፥ ጥላ።

**ጠለሰመ** ግ ጠንቋይ ወይም ደብተራ የሃረግ፥ የሰው ፥... ምስል እያስመሰለ ሳለ ወይም የጥን ቁልና ወይም የአስማት ፅሁፍ ፃፈ።

**ጠልሰም** ስ 1. ከብር ወይም ከሌላ ማእድን ይሰራ የነበረ የሴቶች ያንገት ጌጥ። 2. የተለያየ ስእል ያለበት የጥንቆላና የአስማት ፅሁፍ የያዘ ጥቅል ብራና ወይም ወረቀት።

**ጠለስ** "**ጠለሰ**" ስር ተመ.

**ጠለሸት** "**ጥላሸት**"ን ተመ.

**ጠለቀ**[1] ግ 1. ዘቀጠ፥ ሰጠመ። 2. ወደ ውስጥ ዘልቆ ገባ። 3. በጣም ጎደጎደ። 4. ገባ። *ፀሃይ ጠለቀች።*

**ጠላቂ** ስ ከባህር ወይም ከወንዝ ውስጥ ጠልቆ የሚገባ ዋናተኛ።

**ጣልቃ** በመካከል ወይም በማቋረጥ ወይም አልፎ አልፎ (ያለ፥ የገባ፥ የሚገባ፥...)።

**ጣልቃ ገባ** 1. በማይመለከተው ወይም በማያገባው ነገር ገባ። 2. ያለተራው ወይም ያለቦታው በሌላው መካከል ገባ።

**ጣልቃ ገብ** ቅ በጣልቃ፥ በመካከል የሚገባ።

**ጥልቅ** ቅ 1. ወደታች በጣም ርቀት ያለው (ውቅያኖስ፥ ጉድጓድ፥...)። 2. ሰፊና ዝርዝር የሆነ (እውቀት፥ ምርምር፥...)። 3. ስሜትን የሚነካ። *ጥልቅ ሃዘን ተሰምቶታል።*

**ጥልቅ መርፌ** ስ የጥልፍ መስሪያ የሆነ በጣም ትንሽ መርፌ።

**ጥልቀት** ስ 1. የወደ ውስጥ ወይም የወደታች ርቀት (የባህር፥ የወንዝ)። 2. ወደታች ወይም ወደ ውስጥ ያለ የርቀት መጠን። *የጉድጓዱ ጥልቀት አንድ ሜትር ነው።* 3. መጠን፥ ስፋት (የእውቀት፥ የምርምር)።

**ጥልቅ አለ** ግ 1. ዘው አለ ወይም ድንገት ገባ። 2. በማይመለከተው ነገር ውስጥ ገባ። *በሰው ጉዳይ ጥልቅ ኣትበል።*

**ጥልቅ ብዬ** ቅ በማያገባው ወይም በማይመለከተው ነገር የሚገባ።

**ጠለቀ**[2] ግ ጨለፈ፥ ደነበቀ(ፈሳሽን)። 2. ጨለፈ፥ አወጣ (ወጥን)።

**መጥለቂያ** ስ ውሃን ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገርን ከበርሜል፥ ከእንስራ፥ ከጉድጓድ፥... መቅጃ።

**ጠለቀ**[3] ግ ገባ፥ ተደረገ። *የአበባ ጉንጉን በአንገቷ ጠለቀለት።*

**አጠለቀ** ግ 1. ለበሰ (ለምሳሌ ሹራብ፥ ሱሪ)። 2. አለበሰ (ለሌላ ሰው) ። 3. በብዛት ያዘ፥ አለበሰ። *እከክ አጠለቀው።*

**ተጥለቀለቀ** ግ በብዛት ተሸፈነ፥ ተሞላ (ለምሳሌ በጎርፍ)።

**አጥለቀለቀ** ግ በብዛት ሸፈነ፥ አለበሰ፥ሞላ (ለምሳሌ ጎርፍ፥...)።

**ጠለንጅ(ጠሌንዥ)** ስ ግንዱ አንጓ ያለው አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

**ጠለዘ** ግ መታ፥ ነረተ።

***ጠለጠለ**

**ጥልጥል አለ** ግ ተንጠለጠለ።

**ጥልጥል አደረገ** ግ አንጠለጠለ።

**ተንጠለጠለ** ግ 1. ተሰቀለ። 2. ከፍ ያለ ቦታ ላይ ወጣ፥ ተቀመጠ። 3. አጠረ (ልብስ)። ሊዘንብ ወይም ሊጥል ተቃረበ(ዝናቡ)። 5. ሊወድቅ ወይም ሊፈርስ ትንሽ ቀረው። *ግንቡ ተንጠልጥሏል።* 6. ተጀምሮ ሳያልቅ ወይም ሳይፈፀም ቀረ። *ጉዳዩ እንደተንጠለጠለ ቀረ።*

**ተንጠላጠለ** ግ ወጣ (ዛፍ፥ ገደል፥...ላይ)። 2. በሰው ድጋፍ ወደ አንድ ደረጃ ተሸጋገረ።

**አንጠለጠለ** ግ 1. ሰቀለ። 2. በጆሮ ላይ አደረገ(ጌጥን)። 3 በእጁ ያዘ። *ሻንጣውን አንጠልጥሎ ወጣ።* 4. ስሜትን ያዘ፥ ማረከ፥ አጓጓ። 5. ሳይጨርስ በጅምሩ ተወ።

**እንጥልጥል** ቅ 1. የተንጠለጠለ ወይም ያላለቀ(ጉዳይ) ። 2. ተንጠልጣይ የሆነ፥ (ለምሳሌ የጆሮ ጌጥ)። 3 በአንዳንድ በጎች ወይም ፍየሎች አንገት ላይ ተንጠልጥለው የሚታዩና እንደ ጡት ጫፍ ያሉ አካላት።

**ጠለፈ** ግ 1. አሰናከለ፥ አወላከፈ። 2. በጨርቅ ላይ በክር እየሰፋ አስጌጠ፣ የጥልፍ ስራ ሰራ። 3. አድብቶ በሃይል ወይም በማስገደድ ወሰደ (ልጃገረድን ለትዳር)። 4.ነጥቆ ወሰደ፥ ቀማ (አሞራ)።5.አቅጣጫውን አስለውጦ ወደሚፈለግበት ቦታ ወሰደ (ወንዝን)። 6. አስገድዶ አቅጣጫ አስቀየረ (ብዙውን ጊዜ አውሮፕላንን)። 7. አሰረ(በገመድ)። 8. በሬዲዮ ወይም በስልክ ለሌላ ሰው የሚተላለፈውን መልእክት በምስጢር አደመጠ። 9. የስልክ፥ የኤሌክትሪክ፥... መስመርን ከሌላ መስመር ቀጠለ።

**ጠለፋ** ስ 1. ከመንገድ አስገድዶ በመውሰድ ሚስት የማግባት ድርጊት። 2. አቅጣጫን መለወጥ (ለምሳሌ የወንዝን አፈሳሰስ)።

**የጠለፋ ዋስ** ስ ባለእዳን ለማቅረብ ዋስ የሚሆን ሰው።

**ጥልፍ** ስ በቀሚስ፥ በተለያየ ጨርቅ፥... ላይ በመርፌና በክር ተወሳስቦ የሚሰራ ጌጥ።

**ጥልፍ ቀሚስ** ስ በጥልፍ የተጌጠ የአበሻ ቀሚስ።

**ጥልፍልፍ** ቅ 1. ተወሳስቦ የተሰራ (ለምሳሌ ጫማ)።



ጥልፍ

2. ውስብስብ።

**ተጠለፈ** ግ 1. አቅጣጫው ተለወጠ (የወንዝ አፈሳሰስ)። 2. ተገዶ አቅጣጫ ቀየረ (አውሮፕላን)።

**ተጠላለፈ** ግ ተያያዘ፥ ተወሳሰበ፥ ተቆላለፈ።

**አጠላለፈ** ግ አወሳሰበ፥ አቆላለፈ፥ አስተሳሰረ።

**ጠላ**[1] ስ ከገብስ ወይም ከማሽላ ወይም ከዳጉሳ ወይም ከበቆሎ እንዲሁም ከብቅልና ከጌሾ በቤት ውስጥ የሚዘጋጅ መጠጥ።

**ጠላ አነሳ** የተጣራውን ወይም የጠለለውን ጠላ ከአተላ እየለየ በሌላ እቃ ቀዳ።

**ጠላ ጠመቀ** ጠላ አዘጋጀ።

**የጠላ ቂጣ** ስ በጠላ ጥንስስ ውስጥ የሚገባ ቂጣ።

**ጠላ ቤት** ስ ጠላ የሚሸጥበት ቤት፣ መሸታ ቤት።

**ጠላ**[2] ግ አልወድ አለ፥ ጥላቻ አሳየ።

**ጠላት** ስ 1. የማይወዱት ወይም የሚጠሉት ሰው። 2. ባላጋራ፥ ባላንጣ።3. በአንድ አገር ላይ የዘመተ ወራሪ።

**ጠላት አፈራ/ ገዛ** ጠላት አበጀ።

**ጥል** ስ 1. ጠብ ፥ እምባጓሮ፥ ግጭት። 2. ጠበኛ፥ ኩርፍ።

**ጥለኛ** ቅ የተጣላ፥ ጠበኛ፥ ኩርፈኛ።

**ጥላቻ** ስ የመጥላት፥ ያለመፈለግ፥ ያለመፍቀድ፥ ፀር የመሆን ስሜት።

**ተጠላ** ግ የማይወደድ፥ የማይፈቀድ ሆነ።

**ተጣላ** ግ 1. ጠብ ፈጠረ፥ ተጋጨ፥ ቅራኔ ውስጥ ገባ። 2. አልስማማ አለ፥ አመመ። *የጠጣሁት መጠጥ ተጣላኝ።*

**አጣላ** ግ ጠብ እንዲፈጠር አደረገ፥ አጋጨ።

**አጣይ** ቅ ከወዲያና ከወዲህ ወሬ እያቀበለ ሰውን የሚያጣላ።

**አጥላላ** ግ ዋጋቢስ አድርጎ ተናገረ፥ አጣጣለ፥ አራከሰ፥ አናናቀ።

**አስጠላ** ግ 1. እንዲጠላ አደረገ። 2. አስቀየመ፥ መጥፎ ሆነ፥ የማይፈቀር ወይም የማይወደድ ሆነ።

**አስጠሊታ** ቅ የማያምር፥ ደስ የማይል፥ አስከፊ ወይም አስቀያሚ የሆነ።

***ጠላ**

**ጥላ** ስ 1. ከሰሌን ወይም ከጨርቃ ጨርቅ፥... የሚሰራ የፀሃይና የዝናብ መከላከያ፣ ጃንጥላ። 2. የፀሃይ ጨረር በቀጥታ ያላረፈበት ቦታ። 3. በአንድ አካል ላይ ብርሃን በከፊል ባረፈ ጊዜ ብርሃን ባላረፈበት ወገን በኩል ጥቁር ሆኖ

የሚታይ የአካሉ ምስል:: 4. (ዘይ.) መከታ፥ ተገን :: *ለውዬው የቤተሰቡ ጥላ ነው::*

**ጥላ ሆነበት** የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ከፀሃይ ላይ ቆይቶ የሰውነቱ ሙቀት ገና ያልበረደ፥... ሰው ህመምተኛ ወደተኛበት ክፍል ወይም ቤት ውስጥ ስለገባ ህመምተኛው ህመም ተቀሰቀሰበት፥ ፀናበት(ለምሳሌ የተገረዘ ህፃን፥ የኩፍኝ፥ ... ህመምተኛ)::

**ጥላ በረደ** አየሩ ቀዘቀዘ ወይም ሙቀቱ ቀነሰ (ከቀትር በኂላ የፀሃይ ሙቀት እየቀነሰ በመሄዱ)::

**ጥላ ነኝ** የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ከፀሃይ ሙቀት ላይ የቆየ ሰው፥ ቁስለኛን ወይም ኩፍኝ ወይም ፈንጣጣ፥... የያዘውን ሰው ለመጠየቅ ወደ ህመምተኛው ቤት መግባት እንደማይገባው ለማሳሰብ የሚናገረው አባባል::

**ጥላ ጣለ** 1. የፀሃይ ግለት በረደ:: 2. የፀሃይ ብርሃን በዳመና ወይም በዛፍ ተጋረደ::

**ጥላው ቀለለ** ቀትረ ቀላል ሆነ፥ ሰውነቱ ጭር አለ::

**ጥላ ቢስ** ርጋታ የሌለው፥ ከውካዋ፥ ቀትረ ቀላል፥ ግርማ ሞገስ የሌለው ::

**ጥላወጊ** ስ መተት ወይም አስማት በተደረገበት ሹል ነገር የሰው ጥላ ያረፈበትን ቦታ በመውጋት ሰውየውን ህመምተኛ ለማድረግ ወይም ለመግደል ይችላል የሚባልለት አስማተኛ ወይም ድርጊቱ (መተቱ፥ አስማቱ)::

**አጠላ** ግ 1. ጥላ ጣለ:: 2. ከፀሃይ፥ ከዝናብ ወይም ከብርሃን በጥላ ተከለለ፥ ተጋረደ::

**ጠላቂ** " ጠለቀ[1]" ስር ተመ.

**ጠላት** "ጠላ[2]" ስር ተመ.

**ጠሌንጅ** "ጠለንጅ" ን ተመ.

**ጠል** ስ 1. በሳር ወይም በቅጠል ላይ ተንቆርዞ የሚገኝ ርጥበት ወይም ጤዛ:: 2. ዝናብ፥ ርጥበት:: *ሰማይ ጠል ካላወረደ መሬት ይራባል::* 3. ልምላሜ::

**ጠልሰም** "ጠለሰመ" ስር ተመ.

***ጠመለመለ**

**ጥምልምል** ቅ አቅም ወይም ጥንካሬ የሌለው::

**ተጥመለመለ** ግ 1. ሽባ፥ አቅመቢስ ሆነ:: 2. ተጣጠፈ፥ ተጠቀለለ::

**አጥመለመለ** ግ 1. አዝለፈለፈ፥ አሽመደመደ፤ ሽባ፥አቅመቢስ አደረገ:: 2. አጣጠፈ፥ ጠቀለለ::

**ጠመመ** ግ 1. ጎበጠ፥ ተወላገደ፥ ጋደድ አለ:: 2. (ዘይ.) ከፋ፥ ፈቃደኛ አልሆን አለ፥ ክፉ አሰበ::

**ጠማማ** ቅ 1. ጎባጣ፥ ወልጋዳ፥ ገዳዳ:: 2. (ዘይ.) ክፉ፥ ቅን ያልሆነ::

**ጥመት** ስ (ዘይ.) ክፋት፥ የጠባይ ወልጋዳነት::

**ተጣመመ** ግ ተወላገደ፥ ተንጋደደ፥ ጎበጠ::

**አጣመመ** ግ 1. አንጋደደ፥ አዘነበለ፥ አጎበጠ:: 2 እንዳይሆን፥ እንዳይሳካ አደረገ (ጉዳይን)::

***ጠመረ**

**ጣምራ** ቅ ጥንድ፤ ሁለትነት ያለው::

**ጣምራ ጦር** ስ 1 መንታ ጫፍ ያለው ጦር:: 2. እየተጋገዘ የሚዋጋ ሁለት የጦር ሃይል ::

**ጥምር** ቅ ጥንድ፥ የተጣመረ፥ የተባበረ::

**ጥምር ቃል** ስ ከአንድ በላይ በሆኑ ቃላት የተመሰረተ ቃል፥ ሃረግ::

**ተጣመረ** ግ አንድ ላይ ተደረገ፥ አንድ ሆነ፥ ተባበረ::

**ተጣማሪ** ስ 1. (ሰዋ.) አንድን ስም ለማጉላት በተደራቢ የሚገባ ቃል:: *አበበ ተማሪው ነገ ይመጣል* በሚለው ውስጥ "ተማሪው" ተጣማሪ ነው:: ቅ 2. ተጫፋሪ ፥ ተጓዳኝ፥ አበር::

**አጣመረ** ግ አንድ ላይ አደረገ::

**አጣማሪ** ቅ ቀንጃ፥ ጓደኛ::

**ጠመሰሰ** ግ ጣሰ፥ ገለጠ (ደንን፥ ዳዋን)::

**ጠመቀ[1]** ግ 1. ከተለያየ የእህል አይነት ጠላን ወይም ቢራን አዘጋጀ:: 2. ጨመቀ፥ ጠመዘዘ (እርጥብ ልብስን):: 3. አጣራ፥ ደህናውን ከአተላ ወይም ካአሰር ለየ::

**ጠመቀ[2]** ግ በውሃ ወይም በፀበል ነከረ፥ ዘፈቀ::

**ምጥማቅ** ስ የማጥመቂያ ቦታ ወይም ገንዳ::

**ጥምቀት** ስ (ክር.) 1. ክርስቶስ የተጠመቀ በትን ቀን በማሰብ ጥር 11 ቀን የሚከበር በአል:: 2. ክርስትና መነሳት፥ መጠመቅ::

**ጥምቀተ ባህር** ስ በጥምቀት ዋዜማ ታቦት ከቤተክርስቲያን ወጥቶ የሚያድርበትና የጥምቀት በአል የሚከበርበት ቦታ::


**ተጠመቀ** ግ 1. ክርስትና ተነሳ:: 2. ፀበል ተረጨ፥ ተነከረ::

**አጠመቀ** ግ 1. በውሃ ወይም በፀበል ነከረ፥ ዘፈቀ:: 2. ክርስቲያን አደረገ::

**አጥማቂ** ስ የሚያጠምቅ ካህን::

**ጠመኔ** ስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ለመፃፊያ የሚያገለግል፥ የተለያየ ቀለም ያለው፥ ከኖራ የሚሰራ የፅህፈት መሳሪያ፤ ቾክ::

**ጠመንጃ (ጠበንጃ)** ስ የተለያየ መጠንና አይነት ያለውና ጥይት የሚጎርስ፥ ለጦርነት ወይም ለጥበቃ ወይም ለአደን የሚጠቀሙበት የጦር መሳሪያ::




ጠመንጃ

**ጠመንጃ አቀባበለ** በጠመንጃ ውስጥ ያለውን ጥይት ወደ ቧንቧው አስገብቶ ለተኩስ አዘጋጀ::

**ጠመንጃ አጎረሰ** ጥይት በጠመንጃው ውስጥ አስገባ::

**[የ]ጠመንጃ መፍቻ** ስ ጫፉ ሾል ብሎ ጠፍጠፍ ያለና ብሎኖችን ለመግጠም ወይም ለመፍታት የሚያገለግል መሳሪያ::

**የጠመንጃ ዘንግ** ስ የጠመንጃን ውስጠኛ አካል (ቧንቧን) ለማፅዳት የሚያገለግል ቀጭን የብረት ዘንግ::

***ጠመዘመዘ**

**ጠመዝማዛ** ቅ ቀጥተኛ ያልሆነ፥ ዘወርዋራ (መንገድ:... )::

**ጥምዝምዝ አለ** ግ ተጥመዘመዘ፥ ተጠማዘዘ::

**ተጥመዘመዘ** ግ 1. ቀጥተኛነት የሌለው ወይም ዘወርዋራ ሆነ:: 2. ተሰቃየ፥ ተፍተለተለ፥ ታመመ (ሆድ)::

**አጥመዘመዘ** ግ 1. አመመ (ሆድን):: 2. አፍተለተለ፥ ጠመዘዘ::

**ጠመዘዘ** ግ 1. አጣመመ፥ ቆለመመ:: 2. ጨመቀ፥ ጠመቀ (የረጠበ ልብስን):: 3. አዞረ፥ አቅጣጫ ቀየረ (ለምሳሌ የመኪናን):: 4.(ዘይ.) ሃሳብን፥ አቋምን ቀየረ ወይም አስቀየረ (በማግባባት፥...)::

**ጥምዝ** ቅ የተጠመዘዘ፥ ጥቅል::

**ጥምዝ ወርቅ** ስ እንደሽቦ ያለና የተጠቀለለ ወይም የተጠመጠመ የወርቅ ጌጥ::

**ጠምዛዛ** ስ 1. ቀጭን ሆኖ ጥንካሬ ያለው፥ በቀላሉ የማይሰበር 2. (ዝይ.) ችኮ፥ ገታራ (ሰው)::

**ተጠመዘዘ** ግ 1. ተጣመመ፥ ተቆለመመ:: 2. አቅጣጫ ቀየረ::

**ተጠማዘዘ** ግ ተቆላመመ፥ ተጣመመ::

**አጠማዘዘ** ግ አቆላመመ፥ አጣመመ::

**ጠመዝማዛ** "***ጠመዘመዘ**" ስር ተመ.

**ጠመዥ (ጠመጅ)** ስ ስንዴ የሚመስልና ገለባው በቀላሉ የሚላቀቅ የገብስ አይነት::

**ጠመደ**[1] ግ 1. ቀንበርን በበሬዎች አንገት ላይ በማነቅ በማሰር ለእርሻ አዘጋጀ:: 2. ጀመረ፥ ተያያዘ (ስራን):: 3. ክፉኛ ጠላ::

**ጥማድ** ቅ ጥንድ (በሬ)::

**ተጠመደ** ግ 1. ቀንበር ተጭኖበት ለእርሻ ተዘጋጀ (በሬው):: 2. በስራ ተያዘ ወይም አንድ ነገር በማድረግ ላይ ሆነ:: *በዚት በስራ ተጠምጄል::* 3. ተጠላ፥ በክፉ ሁኔታ የሚተኮርበት ሆነ::

**ተጣመደ** ግ ክፉኛ ተጣላ፥በነገር ተያያዘ::

**አጣመደ** ግ ክፉኛ አጣላ፥ በነገር አያያዘ:: 2. አንድን በሬ ከሌላ በሬ ጋር አቀናጀ ወይም ጠመደ::

**አጣማጅ** ስ 1. አብሮ የሚጠመድ ቀንጃ በሬ:: ቅ 2. አብሮ የሚሰራ፥ የሚሰማራ፥...የስራ ጓደኛ::

**ጠመደ**[2] ግ መሳሪያን፥ ፈንጂን፥ ወጥመድን (እንዲፈነዳ፥እንዲይዝ፥...) አዘጋጅቶ አስቀመጠ::

**ወጥመድ** ስ 1. እንስሳትን ለመግደል ወይም ለመያዝ የሚያገለግል መሳሪያ::2. ሌላን ሰው ለመጉዳት፥ ለማሰናከል፥... የተጠነሰሰ ሴራ፥ ተንኮል፥...::

**ወጥመዱ ያዘለት** ያሰበው ተንኮል ወይም ሸር ተሳካለት::

**ወጥመድ ውስጥ ገባ** 1. በመጥፎ ወይም በተወሳሰበ ነገር ውስጥ ገባ:: 2. የተንኮል ወይም የሴራ ሰለባ ሆነ::

**አጠመደ** ግ 1. ወጥመድን እንዲይዝ፥ ፈንጅን እንዲፈነዳ አድርጎ አዘጋጅቶ አስቀመጠ:: 2. አሳን ከባህር፥ ከወንዝ፥... በመረብ ወይም በመንጠቆ አወጣ ወይም ያዘ:: 3. ሴራ፥ደባ አዘጋጀ::

**ጠመጅ** "ጠመዥን"ን ተመ.

**ጠመጠመ** ግ 1.በራስ ማሰሪያ፥ በሻሽ፥... ራስን ሸፈነ ወይም አሰረ:: 2. አንድን ነገር በሌላ ነገር ላይ እየደጋገመ በማዞር ጠቀለለ (ለምሳሌ ገመድን በእንጨት ላይ):: 3. ተንኮል፥ ሸር፥ ነገር ሰራ::*ነገር ጠመጠመበት::*

**ጠምጣሚ** ቅ 1. ካህን፥ ቄስ:: 2. (ዘይ.) ነገረ ሰሪ::

**ጥምጣም** ስ የ "ጥምጥም"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**ጥምጥም** ስ 1. በራስ ላይ የተደገለለ፥ የታሰረ ሻሽ:: ቅ 2. የተጠመጠመ፥ ጠመዝማዛ የሆነ(መንገድ፥ ነገር፥...)::

**ጥምጥም አለ** ግ 1. ተጠመጠመ:: 2. ሰውነቱ ዳበረ፥ ጎላ፥ ጠነከረ:: *ጥምጥም ያለ ሰውነት::*

**ተጠመጠመ** ግ 1. በአንድ ነገር ላይ በተደጋጋሚ በመዞር ተጠቀለለ፥ ተተበተበ:: 2. አንቆ፥ እቅፍ አድርጎ ያዘ::

**ጠማ**

**ጠማ አለ** ግ 1. በሰለ፥ ጎመራ (እሸት):: 2. መጠጥ አለ::

**ጠማ** ግ 1. አሰኘ፥ አስፈለገ፥ አማረ (መጠጥ፥ ውሃ):: 2. (ዘይ.) ፈለገ፥ አሰኘው:: *ትምህርት ጠምቶታል::*

**ጥማት(ጥም)** ስ (የውሃ፥ የመጠጥ፥ የእውቀት) ፍላጎት::

**ጥም ቆረጠ** አረካ፥ አጠገበ (መጠጥ)።

**ተጠማ** ግ 1. መጠጣት አሰኘው ( ውሃን)። 2. (ዘይ.) አስፈለገ፥ ፈለገ፥ (እውቀት፥ ትምህርት)።

**አስጠማ** ግ የውሃ ጥም አሳደረ፥ አስከተለ።

**ጠማማ** "ጠመመ" ስር ተመ.

**ጠምበለል** "ጠንበለል"ን ተመ.

**ጠምጣሚ** "ጠመጠመ" ስር ተመ.

**ጠሞረ** ግ የተለያየ ቀለማት ያላቸውን ክሮች አንድ ላይ በማድረግ ሸረበ።

**ጥሙር** ቅ የተጠሞረ፥ የተሸረበ (ጥለት፥ ክር)።

**ተጠሞረ** ግ የተለያየ ቀለም ያለው ክር በአንድ ላይ ተሸረበ።

**ጠሚጋ** ቅ ከሲታ።

**ጠረመሰ** ግ 1. ሰረጎደ። 2. ሰበረ፥ ሸረፈ። 3. አስተኛ፥ ጣሰ (ለምሳሌ አጥርን)።

**ተጠረመሰ** ግ 1. ተሰረጎደ። 2. ተሰበረ፥ ተሸረፈ። 3. ተኛ፥ ወደቀ (ለምሳሌ አጥር)።

**ጠረረ** ግ የፀሃይ ሙቀት ጋለ፥ ጠራራ ሆነ።

**ጠራራ(ፀሃይ)** ቅ የእኩለ ቀን ሃይለኛ የፀሃይ ሙቀት ። *በጠራራ ፀሃይ ወዴት ትሄጃለህ?*

**ጠረሰ** ግ 1. ዶለዶመ፥ ደነዘ፥ አልቆርጥ አለ (ስለት)። 2. አላኘክ አለ፥ የሚሰቀጥጥ ስሜት ፈጠረ (ጥርስ)።

**ተጣረሰ** ግ 1. እርስ በእርስ ተደባደበ። 2.እርስ በርሱ ተፋጨ፥ ተጋጨ (ለምሳሌ ጥርስ)።3. ተቃወሰ፥ ተበላሸ (ክርክር፥ የነገር ስልት)።

**አጣረሰ (አንጣረሰ)** ግ 1. አማታ፥ አደባደበ። 2. አቃወሰ፥ አፋለሰ፥ አበላሸ (ክርክርን፥ የነገር ስልትን) ።

**ጠረሰመ** ግ ጠረመሰ፥ሰበረ፥ አደቀቀ።

**ጠረቀ** ግ 1. ጠረነቀ፥ አጥብቆ አሰረ። 2. ቸነከረ። 3. (ዘይ.) ብዙ አወራ፥ አወጋ። *ለግፉን እንፈራጠ ወሬውን ሲጠርቅ ዋለ።* 4. (ዘይ.) እስኪጠግብ በላ።

**ጠርቅ** ቅ (ዘይ.) ብዙ የሚበላ፥ ሆዳም።

**ተጠረቀ** ግ ተጠረነቀ፥ ጠብቆ ታሰረ።

**ጠረቀመ** ግ 1.ወጋ፥ ሰካ። *ጸሸሁ ጠረቀመበት።* 2. አጥብቆ አሰረ። 3. ዝም አሰኘ። 4. አጥብቆ ዘጋ + ቆለፈ። 5. በጥፊ መታ፥ አጠናፈረ። *በጥፊ ጠረቀመበት።*

**ተጠረቀመ** ግ ተሰካ፥ ገባ። *ጸሸሁ ተጠረቀመበት።* 2. ዝም አለ። 3. ተዘጋ፥ ተቆለፈ።

***ጠረቀመ**

**ጥርቃሞ** ቅ 1. ከየትም ከየትም የተሰበሰበ። 2. ፋይዳ ቢስ፥ እርባና የለሽ።

**ጥርቅም** ቅ የተጠራቀመ፥ ከተለያየ ቦታ የተሰበሰበ፥ ስብስብ።

**ጥርቅምቅም** ቅ ከየቦታው የተሰበሰበ፥ ግሳንግስ።

**ተጠራቀመ** ግ 1. ተከማቸ፥ ተሰበሰበ። 2.ቀስ በቀስ ብዙ ሆነ።


**አጠራቀመ** ግ 1. አከማቸ፥ሰበሰበ፥ አስቀመጠ (ለምሳሌ ገንዘብን)። 2. አንድ ላይ አስቀመጠ።

**ጠረቃ** ግ ዳበረ፥ ወፈረ (ሰውነቱ)።

**አጠረቃ** ግ አዳበረ፥ አወፈረ።

**ጠረቆሸ** ግ ሸነቆረ፥ ቀደደ።

**ጠረበ** ግ 1. በመጥረቢያ፥ በመሮ፥...እየታገዘ አስተካከለ፥የሚፈለገውን ቅርፅ እንዲይዝ አደረገ (እንጨትን፥ ድንጋይን)። 2. (ዘይ.) ነቀፈ፥ ተቸ፥ ወረፈ(ሰውን)። *በሰላ ሂስ ጠረበው።*



**መጥረቢያ** ስ የእንጨት መቁረጫ ወይም መፍለጫ ምሳር።

መጥረቢያ

**ጠራቢ** ቅ ድንጋይን፥ እንጨትን በመጥረብ ወይም በመቆርቆር፥... ቅርፃ ቅርፅ የሚያወጣ (ሰው)።

**ጠርብ** ስ ለቤት ወይም ለአጥር፥ መስሪያ የሚያገለግል ረጅም ፍልጥ።

**ጠርብ ያህላል** ረጅምና ወፍራም ነው።

**ጥራቢ** ቅ ድንጋይ፥ እንጨት፥... ሲጠረብ የሚወድቅ ስብርባሪ፥ ድቃቂ፥ ፍቅፋቂ።

**ጥርብ** ቅ የተጠረበ ወይም የተስተካከለ (ድንጋይ፥ እንጨት)።

***ጠረበበ**

**ተንጠረበበ** ግ 1. ተንደረበበ፥ ጢም ያለ ሆነ እስከ አፉ ሞላ (ሰፍር)። 2. አኮረፈ። 3.ተንጠረዘዘ፥ ዝናብ ሊጥል ደረሰ (ደመና)።

**አንጠረበበ** ግ በጣምሳይሞላ በድርበቡ ሰፈረ።

**ጠረነቀ** ግ 1. አጥብቆ አሰረ፥ ቀፈደደ። 2. መታ፥ ጠሰቀ።

**ጠረን** ስ የአካል ወይም የሰውነት ሽታ።

**ጠረንገሎ(ጠረንገላ)** ቅ ወደል፥ ጠብደል።

***ጠረወዘ**

**ጠርዋዛ** ቅ ከልዋሳ፥ ገልዋዳ።

**ጥርውዝ ጥርውዝ አለ** ግ ወዲያ ወዲህ ተንከላወሰ፥ ተንገላወደ።

**ተንጠራወዘ** ግ ተንከላወሰ፥ ተንገላወደ።

**አንጠራወዘ** ግ አንከላወሰ፥ አንገላወደ።

**ጠረዘ** ግ 1. የተባረባቸውን ወይም ያልተባረባቸውን ብትን ወረቀቶች ወይም የብራና ቅጠሎች በመፅሃፍ መልክ አዘጋጀ (ወረቀቶቹን ወይም የብራና ቅጠሎቹን አንድነት በመስፋት፥ በማጣበቅ፥...)። 2. ያረጀ ወይም ጥራዙ የተገነጠለ መፅሃፍን እንደገና አደሰ፥ ደጎሰ። 3. አሰረ፥ ጠፈረ(ለምሳሌ የተበታተኑ እቃዎችን አንድነት በማድረግ)። 4. ለጎመ (እንደ አገልግል፥ ቁና፥.. ያለ የስፌት እቃን)። 5. መታ፥ ጠረቀመ።

**ጠራዥ** ስ የጥራዝ ስራ ባለሙያ።

**ጠርዝ** ስ የአንድ አካል ጫፍ፥ ዳር።

**ጠርዝ አስያዘ** ስርአት፥ መስመር አስያዘ (ነገሩን)።

**ጥራዝ** ስ 1. የመፅሃፍ ቅርፅ (በአንድ ላይ የተያያዘ ወይም የተሰፋ ብራና ወይም ወረቀት)። 2. ብትን ወረቀቱ ወይም ብራናው የተያያዘበት ስፌት።

**ጥራዝ ነጠቅ** ቅ 1. ስለአንድ የእውቀት ዘርፍ ጠለቅ ያለ ትምህርት ሳይኖረው ወይም በደንብ ሳያውቅ ወይም ሳይማር በሚገባ እንደተማረና እንደሚያውቅ ሆኖ የሚያወራ። 2. (ዘይ.) ያልተረጋገጠ፥ ተባራሪ (ወሬ)።

**ጥርዝ** ሰውነቱ ድድር ያለ አጭር ሰው።

**ተጠረዘ** ግ ታሰረ፥ ተተበተበ፥ ተጠፈረ፥ ተሸፈነ።

***ጠረዘዘ**

**ጠርዛዛ(ጠረዘዝ)** ቅ 1. ሆደ ቀብዳዳ፥ ዘርጣጣ። 2. (ዘይ.) ቀብራራ፥ ኩሩ።

**ተንጠረዘዘ** ግ 1. ተንቀበደደ፥ ተንዘረጠጠ። 2. (ዘይ.) ኮራ፥ ተንቀባረረ።

**አንጠረዘዘ** ግ 1.አንቀበደደ፥ አንዘረጠጠ።

**ጠረገ** ግ 1. አፀዳ፥ ወለወለ፥ አጠራ። 2. አጨደ፥ ከስሩ ቆረጠ። 3. ሟጠጠ፥ ጨርሶ ወሰደ። 4. ጨረሰ፥ ገደለ። *ተላላፊ በሽታ ገብቶ ጠረጋቸው።* 5. ጨርሶ፥ ሟጦ በላ።6. በሃይል መታ (በዱላ)።

**መጥረጊያ** ስ እጀታ እንዲኖረው ተደርጎ ከሰሌን ወይም ከናይለን ክር ወይም ከቃጫ፥... የሚሰራና ለቤት ማፅጃነት የሚያገለግል መሳሪያ።

**ጠራጊ** ስ ቤት ወይም መንገድ የሚያፀዳ።

**ጥራጊ** ስ 1. አስፈላጊ ባለመሆኑ ከተለያዩ ቦታዎች (ከቤት፥ ከግቢ፥...) ላይ እየተጠረገ እንዲወገድ የሚደረግ ቆሻሻ።2.በድስት ወይም በሰሃን ውስጥ የቀረ ሙጣጭ ወጥ ወይም የምግብ ፍርፋሪ። 3. (ዘይ.፥ስድብ) የማይረባ፥ ምናምንቴ (ሰው)።

**ጥርጊያ** ስ 1. የተጠረገ፥ አባጣ ጎባጣው የተስተካከለ፥ የተደለደለ ሰፊ መንገድ፥ ጎዳና። 2. አንድ ነገር ለመስራት ወይም ለማከናወን አትጣጫ የማስያዝ ጅማሮ።

**ጥርግ አለ** ግ 1. እብስ፥ ጭልጥ ብሎ ሄደ።2.ሙልጭ ብሎ ሄደ።

**ተጠረገ** ግ እብስ ብሎ ሄደ። *ተጠርጎ ሄደ:*

**ተጠራረገ** ግ ተያይዞ ሄደ።*ተጠራርገው ሄዱ።*

**ጠረጠረ**[1] ግ 1. አንድ ነገር ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል ብሎ አሰበ፤ ሰጋ፥ፈራ።2. እምነት አጣ ወይም ሳይተማመን ቀረ።

**ጠርጣሪ** ቅ 1. ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል ብሎ የሚያስብ፥ የሚገምት። 2. ጎበዝ፥ ንቁ።

**ጠርጣራ** ቅ ንቁ፥ ጠንቃቃ።

**ጥርጣሬ** ስ አንድን ነገር አምኖ አለመቀበል፥ ማመንታት፥ መስጋት፥ መወላወል።

**ጥርጥር** ስ 1. እርግጠኛ ያለመሆን ሁኔታ። 2. ስጋት፥ እምነት ማጣት።

**ጥርጥር የለውም** እርግጥ ነው።

**ተጠረጠረ** ግ አንድ ነገር አድርጓል ወይም ፈፅሟል ተብሎ ታሰበ፥ ተገመተ፥ ታማ።

**ተጠርጣሪ** ቅ አንድን ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የሚገመት።

**አይጠረጠርም** 1. እርግጥ ነው። *ፈተናውን እንደሚያልፈው አይጠረጠርም።* 2. እምነት የሚጣልበት ወይም ታማኝ ነው።

**ተጠራጠረ** ግ 1. ሰጋ፥ ፈራ፥ ይሆናል ወይም አይሆን ይሆናል ብሎ አሰበ። 2. አመነታ፥ አወላወለ፥ እምነት አጣ።

**ተጠራጣሪ** ቅ 1. እምነት የሌለው። 2. ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል ብሎ የሚያስብ።

**አጠራጠረ** ግ እውነተኛ ወይም እርግጠኛ መሆኑ አጠያያቂ ሆነ።

**አጠራጣሪ** ቅ ሙሉ በሙሉ የማይታመንበት፥ አጠያያቂ።

**ጠረጠረ**[2] ግ 1. ፈለፈለ፥ሽፋኑን ወይም ገለፈቱን አነሳ (የባቄላን፥ የሽንብራን፥...)። 2. እየፈለፈለ በላ (የባቄላን እሹቅ ወይም እሸት፥...)።

**ጥርጣሬ** ስ የሽንብራ ወይም የባቄላ ፍሬ ሽፋን፥ ገለባ፥...።

**ተንጠረጠረ** ግ 1. ተንቀረቀበ፥ የሚፈለገው ከማይፈለገው እንዲለይ ተደረገ(ለምሳሌ እንክርዳዱ ከስንዴ)። 2. በብርድ፥ በድንጋጤ ምክንያት ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ።

**አንጠረጠረ** ግ 1. አንቀረቀበ፥ ፍሬውን ከገለባ ለየ። 2. አንቀጠቀጠ፥ አንዘፈዘፈ (ብርድ፥ ድንጋጤ)። 3. (ዘይ.) አብጠረጠረ፥ በዝርዝር ተነተነ። *አንጠርጥሮ ያውቀዋል።*

**እንጥርጣሬ** ስ ብጣሪ፥ እንቅጥቃጭ።

**ጠረጠሰ** ግ 1. ዶለዶመ፥ ደነዘ:: 2. (ዘይ.) አረጀ፥ ጨረጨሰ::

**ጠርጣሳ** ቅ 1. የዶለዶመ፥ የደነዘ:: 2. (ዘይ.) ያረጀ፥ የጨረጨሰ::

**ጥርጥስ** ቅ ቾርቾፍ፥ ስለት አልባ::

**ጠረጴዛ** ስ ላዩ ጠፍጣፋና ክብ ወይም ባለአራት ማእዘን የሆነ፥ በአብዛኛው አራት ወይም ሶስት እግር ያለው፥ ከእንጨት ወይም ከብረት፥.. የሚሰራና ለእቃ ማስቀመጫ ወይም ለመመገቢያ፥ ለመፃፊያ፥...የሚያገለግል የቤት ቁሳቁስ::

**በጠረጴዛ ዙሪያ** በውይይት፥ በድርድር:: *ልዩነትን በጠረጴዛ ዙሪያ መፍታቱ ስልጣኔ ነው::*

**የጠረጴዛ ልብስ** ስ ለጠረጴዛ እንደሽፋንና እንደጌጥ ሆኖ የሚያገለግል ጨርቅ ወይም ፕላስቲክ::

**የጠረጴዛ ሰአት** ስ በጠረጴዛ ላይ የሚቀመጥ ተለቅ ያለ ሰአት::

**የጠረጴዛ ኪስ** ስ የጠረጴዛ አካል ሆኖ ከጠረጴዛው ጋር አብሮ የሚሰራ የእቃ ማስቀመጫ ክፍል፤ መሳቢያ::

**የጠረጴዛ ኳስ** ስ ሁለት ሁለት ወይም አንዳንድ ሰው የያዙ ሁለት ቡድኖች መረብ አግድም መሃሉ ላይ በተወጠረበት ጠረጴዛ ላይ ለዚሁ የተሰራ ኳስን በራኬት እየመቱ ኳሷን በተቃራኒ ቡድን ክልል ላይ ለማሳረፍ የሚደረግ የውድድር ጨዋታ:: ጨዋታው የሚካሄድበትም ኳስ በዚሁ ስም ይጠራል::

**ጠረፈ** ግ አሰረ፥ ቀረቀበ፥ ጠፈረ::

**ጠረፍ** ስ 1. ወሰን፥ ድንበር:: 2. ዳር አገር::

**ጠረፍ ጠባቂ** ስ የሃገርን ዳር ድንበር የሚጠብቅ ወይም የሚያስከብር ወታደር::

**ጠራ**[1] ግ 1. እከሌ በማለትና ስምን በመጥቀስ ድምፅ አሰማ፥ ተናገረ:: 2. ተናጋሪው ወዳለበት እንዲመጣ አደረገ ወይም ጠየቀ ወይም ና ወደ እኔ አለ:: 3.ሰየመ፥ ስም አወጣ:: 4. እንዲመጣ ወይም እንዲካፈል ጋበዘ፥ ጠየቀ (ለግብዣ፥ ለስብሰባ፥...):: 5. አቃጨለ፥ የደወል ድምፅ አሰማ:: *ስልኩ እየጠራ ነው::*

**መጥሪያ** ስ 1. ከፍርድ ቤት ወይም ከፖሊስ ጣቢያ ወይም ከቀበሌ፥.. ተከሳሽን ወይም ምስክርን ለማቅረብ ወይም ለመጥራት የሚሰጥ ደብዳቤ:: 2. ሲጫኑት ድምፅ የሚያሰማ ወይም የሚደውልና ለጥሪ የሚያገለግል ደወል::

**ጥሪ** ስ 1. ስምን በመጥቀስ መጥራት:: 2. በአንድ አይነት ጉዳይ ወይም ስነስርአት ላይ በመገኘት የጉዳዩ ተካፋይ ወይም ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚጠይቅ መልእክት ወይም ግብዣ::

**የጥሪ ወረቀት** ስ (ለግብዣ፥ ለስብሰባ፥...) እንዲመጡ ወይም እንዲሳተፉ ለማድረግ የሚሰጥ የግብዣ ወረቀት ወይም ደብዳቤ::

**ተጠራ** ግ 1. ተናጋሪው ወዳለበት ወይም መልእክቱን ወደአስተላለፈው ዘንድ እንዲሄድ ተነገረው:: 2. ስም ወጣለት፥ ተሰየመ፥ ተባለ:: *ከተማው አዲስ አበባ ተባሉ ተጠራ::* 3. እንዲመጣ ወይም እንዲካፈል ተጋበዘ::

**ተጠሪ** ስ ወኪል፥ እንደራሴ::

**ተጣራ** ግ ጮክ ብሎ ስምን ጠራ ወይም እገሌ አለ::

**ተጠራራ** ግ አንዱ ሌላውን እየጠራ ተሰባሰበ::

**አስጠራ** ግ ስምን በጥሩ ወይም በመጥፎ ነገር አስነሳ::

**ጠራ**[2] ግ 1. ፀዳ፥ ንፁህ ሆነ:: 2. ጠለለ፥ የተጣራ ሆነ:: 3. ወለል አለ፥ ደመና የሌለው ሆነ (ሰማይ)::

**ጥሩ** ቅ 1. ንፁህ፥ የተጣራ:: 2. ደህና፥ ቆንጆ፥ ጥራት ያለው:: 3. መልካም፥ ግለፊያ:: 4. እሺ፥ ይሁን ለማለት የሚያገለግል ቃል::

**ጥራት** ስ ጥሩነት፥ ብቃት (የእህል፥ የስራ፥ የእቃ፥...)::

**ተጣራ** ግ 1. ንፁህ ሆነ፥ ጠራ:: 2. ተረጋገጠ፥ እውነቱ ታወቀ (ነገር)::3.ተሸጠ፥ አለቀ (ሸቀጥ፥...):: 3. ልቅም ተደርጎ ተሰራ(ተዝረክርኮ የነበረው)::

**አጠራ** ግ 1. አፀዳ፥ ንፁህ አደረገ:: 2.አጠለለ፥ አጣራ:: 3.ሳያዝረከርክ ልቅም አድርጎ ሰራ(ተዝረክርኮ የነበረውን)::

**አጣሪ** ስ ቾርቻሪ ነጋዴ (ልዩ ልዩ ሸቀጦችን)::

**አጣራ** ግ 1. መጠጥን ከተጠመቀበት ወይም ከተጣለበት ወደ ሌላ እቃ እያጠለለ ገለበጠ:: 2. አረጋገጠ፥ እውነቱን አወቀ:: 3. ጨርሶ ሸጠ( ሸቀጣ ሸቀጥን፥...):: 4. ልቅም አድርጎ ሰራ::

**ማጣሪያ** ስ 1. ማጥለያ፥ ወንጠፍት:: 2. (ስፖ.) ለመጨረሻ ውድድር የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎችን ለመለየት የሚደረግ ውድድር::

**[የ] ማጣሪያ ሽያጭ** ስ የነበረውን ሸቀጥ በሙሉ በሌላ ለመተካት ወይም የንግድ ዘርፉን ለመለወጥ፥... ሲፈለግ እቃዎቹን ከመደበኛ ዋጋቸው በመቀነስ የሚካሄድ ሽያጭ::

**ጠራራ** "ጠረረ" ስር ተመ.

***ጠራራ**

**ተንጠራራ** ግ ቁመቱ የማይደርስበት ቦታ ለመድረስ እጁን ዘረጋ:: 2. ሰውነቱን በመለጠጥ ወይም በመዘረጋጋት አፍታታ:: 3. ተኩራራ፥ ያልሆነውን ለመሆን ሞከረ::

**አንጠራራ** ግ 1. እጅና እግሩን በሃይል በመዘርጋት ለማስረዘም ሞከረ (አንድ ነገር ለመንካት ወይም አንድ ነገር ላይ ለመድረስ)::

2. አኩራራ::

**ጠራቢ** "ጠረበ" ስር ተመ.

***ጠራወዘ**

**ጠርዋዛ** ቅ ከልዋሳ::

**ጥርውዝ ጥርውዝ አለ** ግ ወዲያ ወዲህ ተንከላወሰ::

**ተንጠራወዘ** ግ ተንከላወሰ::

**አንጠራወዘ** ግ አንከላወሰ::

**ጠራዥ** "ጠረዘ" ስር ተመ.

**ጠራጊ** "ጠረገ" ስር ተመ.

**ጠር** " *ፀረረ" ስር "ፀር" ን ተመ.

**ጠርሙስ** ስ ከመስታወት መሳይ ነገር የሚሰራ ከአፉና ከአንገቱ ጠባብ የሆነ የፈሳሽ መያዣ::

**ጠርቅ** "ጠረቀ" ስር ተመ.

**ጠርቡሽ** ስ በራስ ላይ የሚደረግ የቆብ አይነት::

**ጠርብ** "ጠረበ" ስር ተመ.

**ጠርዋዛ** "*ጠረወዘ" ስር ተመ.

**ጠርዛዛ** "*ጠረዘዘ"ስር ተመ.

**ጠርዝ** "ጠረዘ" ስር ተመ.

**ጠርጣሪ** "ጠረጠረ[1] "ስር ተመ.

**ጠርጣራ** ዝ.ከ.

**ጠርጣሳ** "ጠረጠሰ" ስር ተመ.

**ጠሮ**

**ጠሮ ሃረግ** ስ ቀርና ቅርጫት የሚሰራበት ጠንካራ የሆነ የሃረግ አይነት::

**ጠሮ ነፋስ** ስ ሃይለኛ አውሎ ነፋስ::

**ጠሰቀ** ግ 1. አጥብቆ አሰረ፥ ቀፈደደ:: 2. በብዛት በላ:: 3. አመቀ፥ ጠቀጠቀ:: 4. ነረተ ፥ ደሰቀ::

**ጥስቅ** ቅ የሞላ::

**ጥስቅ ያለ ሰውነት** ስ ሙሉ ሰውነት::

**ጥስቅ አደረገ** ግ 1. ቀስር ያዘ፥ አላስተነፍስ አለ (ህመም):: 2. ጠሰቀ::

**ጥስቅ አድርጎ በላ** በደንብ አድርጎ በላ::

**ጠሰጠሰ** ግ 1. ነቀዘ፥ ጠነጠነ (እንጨት):: 2. (ዘይ.) አረጀ፥ ጨረጨሰ::

**ጠስጣሳ** ቅ ያረጀ፥ የጨረጨሰ::

**ጠቀለለ** ግ 1. ሸበለለ፥ ጠመጠመ:: 2. ሰበሰበ፥ አንድ አድርጎ ያዘ:: 3. መትቶ ጣለ:: 4. ህጋዊ ባልሆነ ግንኙነት የደፈራትን ልጃገረድ ወይም ያስረገዛትን ሴት አገባ:: 5. ጨመረ፥ አካተተ:: *ማህበራችን ወጣቶችንም ይጠቀልላል::* 6. የጋራ የነበረን ነገር ለብቻው ወይም ለግሉ አደረገ::

**መጠቅለያ** ስ ሴቶች ፀጉራቸውን የሚጠቀልሉበት ከፕላስቲክ ወይም ከብረት የተሰራ እቃ፤ ቢጎዲን::

**ጠቅላላ** ተው.ግ. ሁሉም፥ በሙሉ:: ቅ 2. ሁሉንም የሚይዝ ወይም የሚያካትት::*ጠቅላላ ሪፖርት::*

**በጠቅላላ** ተው.ግ. 1. በሙሉ:: 2. ሙሉ በሙሉ በአንድነት፥ በአጠቃላይ፥ በድምሩ::

**ጠቅላላ ምርጫ** ስ 1. ሁሉም አባላት የተሳተፉበት ምርጫ:: 2. አጠቃላይ የአመራር አባላትን ለመምረጥ የሚካሄድ ምርጫ::

**ጠቅላላ ውጤት** ስ የተገኘው ሁሉም ውጤት በድምሩ::

**ጠቅላላ ገቢ** ስ የተገኘው ሁሉም ገቢ በድምሩ::

**ጠቅላላ ጉባኤ** ስ ሁሉንም አባላት የሚያጠቃልል ወይም የሚወክል ስብሰባ ወይም ጉባኤ::

**ጠቅላይ** ቅ 1. የበላይ፥ ከፍተኛ:: 2. በስሩ የተለያዩ ነገሮችን፥ ክፍሎችን የሚያካትት::

**ጠቅላይ ሚኒስትር** ስ የአንድን ሃገር መንግስት ወይም መስተዳድር የሚመራ የሚኒስትሮች ሰብሳቢ::

**ጠቅላይ ግዛት** ስ ክፍለ ሃገር (ከ1966 ዓ.ም. በፊት ይባል የነበረ)::

**ጥቅል** ቅ 1. የተጠቀለለ፥ ሽብልል:: ስ 2. በወፍራሙ የተበካ ሊጥ:: 3. ድምር:: 4. በአንድነት የተጠቀለለ ወይም የታሰረ ነገር፥ እቃ፤ እስር::

**የጥቅል ስም** ስ (ሰዋ.) ብዙ ነገሮች በአንድነት ተጠቃለው የሚጠሩበት ስም(ለምሳሌ መንጋ፥ እፅዋት)::

**ጥቅል ጎመን** ስ ቅጠሉ በአንድነት እየተጠቀለለና እየተነባበረ የሚበቅል፥ መልኩ ነጣ የሚልና ቅርፁ ድቡልቡል የሆነ የጎመን አይነት::



ጥቅል ጎመን

**ተ ጠ ቃ ለ ለ** ግ 1.ተፈፀመ፥ተከናወነ፥አለቀ:: *ሴሚናሩ ተጠቃለለ::* 2. አንድ ላይ ተደመረ፥ ተካተተ::

**አጠቃለለ** ግ 1. አንድ ላይ አደረገ፥ አካተተ:: 2.ደመደመ (ንግግርን፥...)::3.የግሉ ወይም የብቻው አደረገ::

**ማጠቃለያ** ስ 1. ማሳረጊያ፥ ማብቂያ፥ መጨረሻ:: 2. መደምደሚያ::

**አጠቃላይ** ቅ 1. ሁሉንም አካቶ የሚይዝ ወይም የሚያሳትፍ:: 2. ሁሉንም የሚመለከት፥ የሚያቅፍ፥...:: 3.ዝርዝር ያልሆነ::

**በአጠቃላይ** ተው.ግ. 1. በድምሩ፥ በሙሉ::

2. በጥቅሉ፥ ባጭሩ (ቀደም ሲል የተገለፀው ወይም የተዘረዘረው ነገር ሲጠቃለል ወይም በአንድነት ሲሰበሰብ)።

**ጠቀመ**[1] ግ 1. ረዳ፥ አገለገለ፥ በጀ። 2. በቃ፥ አጠገበ።

**ጠቃሚ** ቅ ጥሩ፥ ተፈላጊ፥ የሚያገለግል።

**ጥቅም(ጠቀሜታ)** ስ 1. እርባና፥ ፋይዳ፥ ረብ። 2. አገልግሎት። 3. ትርፍ ወይም ውጤት።

**ከጥቅም ውጪ ሆነ** ተበላሸ፤ ከብልሽት የተነሳ አገልግሎት የማይሰጥ ሆነ።

**ከጥቅም ውጪ አደረገ** አበላሸ፥ አሰናከለ።

**ጥቅም አሳዳጅ** ለግል ጥቅሙ የሚሯሯጥ።

**ጥቅም የለውም** 1. ምንም አያገለግልም።2. ትርፍ የለውም።

**ተጠቀመ** ግ 1. ተገለገለ።*ረቂቁን ለመፃፍ እርሳስ ተጠቅመናል።* 2. ረብ፥ ፋይዳ፥ ትርፍ አገኘ።

**ተጠቃሚ** ቅ 1. ተገልጋይ። 2. ረብ፥ ፋይዳ፥ ትርፍ የሚያገኝ።

**ተጠቃቀመ** ግ ተረዳዳ፥ ተጋገዘ (አንዱ ሌላውን በመጥቀም)።

**አጠቃቀም** ስ 1. በአንድ ነገር ወይም መሳሪያ ለመገልገል የሚያስችል እውቀት፥ ችሎታ (የአከፋፈት ፥ የአዘጋግ፥...)። 2. አንድ ነገር በአገልግሎት ላይ የሚውልበት መንገድ፥ ዘዴ፥ እውቀት። *የቃላት አጠቃቀም።*

**ጠቀመ**[2] ግ ሰፋ፥ ደረተ፥ ጣፈ።

**ጠቀሜታ** "ጠቀመ[1]" ስር "ጥቅም"ን ተመ.

**ጠቀራ(ጠቀሮ)** ስ ጥላሸት፥ ጥቀርሻ።

**ጠቀራም** ቅ ጥቀርሻ የለበሰ፥ የጠቆረ።

**ጠቀሰ**[1] ግ 1. ጠራ፥ አመለከተ (በእጅ፥በአይን)። 2. ለመረጃ ወይም ለምስክርነት ከንግግር፥ ከፅሁፍ፥... ያገኘውን እንዳለ ቀድቶ ወይም ወስዶ በቃል ወይም በፅሁፍ አቀረበ (ምንጩን ጠቅሶ)።

**ጥቅስ** ስ 1. ለመረጃነት፥ ለምስክርነት፥... ከአንድ መፅሃፍ ወይም ንግግር ውስጥ የተወሰደ ፅሁፍ፥ አባባል።

**ጥቅሻ** ስ በአይን ወይም በእጅ የሚደረግ ጥሪ ወይም ምልክት።

**ጠቀስ አደረገ** ግ በምልክት ወይም በጥቅሻ ጠራ ።

**ተጠቃቀሰ** ግ 1. በጥቅሻ መልእክት፥ ሃሳብ ተለዋወጠ። 2.ተጠራራ። *ሰላቱ ሰዎች ከመካከላችን ተጠቃቅሰው ሄዱ።*

**ተጠቃቀሱበት** በመጠቃቀስ አሽሟጠጡት (አጠገባቸው ያለውን ሰው)።

**ተጣቀሰ** ግ ተመላከተ፥ ተወራረሰ።

**ጠቀሰ**[2] ግ ነከረ (ወጥን በእንጀራ፥ ቀለምን በብርእ ፥...)።

**አጠቀሰ** ግ እንጀራን ወይም ዳቦን በወጥ፥ በተልባ፥... ነከረ (ለመብላት) ወይም ብርእን ቀለም ውስጥ ነክሮ አወጣ (ለመፃፍ)።

**አጠቃቀሰ** ግ እንጀራን ወይም ዳቦን ወጥ አስነካ (ለመብላት)።

**ጠቀጠቀ** ግ 1. አመቀ፥ አጨቀ። 2. ዘጋ፥ ወተፈ(ቀዳዳን)። 3. አፍንጫን አፈነ፥ አላስተነፍስ አለ(ጉንፋን)። 4. ረገጠ፥ ደቀደቀ፥ ረመረመ። 5. ዘርዛራ፥ሽክሻካ እንዳይሆን አደረገ (ወንፊትን፥ ጨርቅን)። 6. ብዙ ቦታ በሳ (በሹል ነገር)። 7. አለፍ አለፍ እያለ ወጋ ወጋ አደረገ፥ አስጌጠ (ዳቦን፥ ቂጣን)። 8. (ዘይ.) አብዝቶ ጎረሰ፥በጣም እስኪጠግብ በላ። 9. (ዘይ.) ነካካ (በነገር)።

**ጠቃጠቆ** ቅ 1. የነጠብጣብ ምልክት፥ ዝንጉርጉር፤የተለያዩ ቀለማት ስብጥር። 2. አልፎ አልፎ የጠባሳ ምልክት ያለበት። *ፈንጣጣ ያቆሰለችው ፊቱ ጠቃጠቆ ሆኖ ቀረ።*

**ጥቅጥቅ** ቅ 1.ዘርዛራ ወይም ሽክሻካ ያልሆነ። (ጨርቅ፥ ወንፊት።) 2. ተቀራርቦ የበቀለ፥ ጭፍግ ወይም ጭፍቅ ያለ (ለምሳሌ (ጫካ)።

**ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ** ድፍን ያለ፥ እይታን ፈፅሞ የሚከለክል፥ ድቅድቅ ያለ ጨለማ።

**ጥቅጥቅ አደረገ** ግ ጠቀጠቀ።

**ጥቅጥቅ አድርጎ ካደ** ፈፅሞ ካደ ።

**ተጠቀጠቀ** ግ 1. ተዘጋ ፥ ተደፈነ (አፍንጫ)። 2. ዘርዛራ እንዳይሆን ተጠጋግቶ ተሰራ (ሹራብ፥ ጨርቅ፥..)።

**ጠቃ** ግ ሰረረ፥ እንስቲቷ ላይ ወጣ፥ መታ(ለእንስሳት)።

**ጠቅ አደረገ** ግ ወጋ።

**ተጠቃች** ግ ተሰረረች (ጊደር)።

**አስጠቃ** ግ አሰረረ።

***ጠቃ**

**ጥቃት** ስ 1. በደል፥ ግፍ፥ ጭቆና። 2. የሃይል ርምጃ (የጦርነት)።

**ጥቃተኛ** ቅ ግፍ፥ በደል የተፈፀመበት።

**ተጠቃ** ግ 1. ግፍ፥ ጭቆና ደረሰበት፥ ተበደለ። 2. ሽንፈት ደረሰበት።

**አጠቃ** ግ 1. በደለ፥ ግፍ አደረሰ፥ ጨቆነ (ሰውን)። 2. በውድድር ወይም በጦርነት አሸነፈ፥ የበላይነትን ያዘ።

**አጥቂ** ስ 1. በደል፥ ግፍ፥ ጭቆና የሚያደርስ።2.(በውድድር፥በጦርነት፥...) የበላይነትን የያዘ፤ ያየለው ወገን። 3. በእግር ኳስ

ጨዋታ ጊዜ በተቃራኒው ቡድን ላይ ግብ ለማስገባት በፊት ለፊት መስመር የሚጫወት ተጫዋች።

**አስጠቃ** ግ 1. በደል፥ ግፍ እንዲደርስ አደረገ ወይም መንገድ ከፈተ። 2. ጥቃት እንዲመጣ ምክንያት ሆነ።

**ጢቃጠቆ** "ጠቀጠቀ" ስር ተመ.

**ጠቅላላ** "ጠቀለለ" ስር ተመ.

**ጠቅላይ** ዝ.ከ.

**ጠቆመ** ግ 1. አመለከተ፥ አሳየ፥ ነገረ። 2. ነካ፥ ወጋ፥ ደነቆለ። 3. የሚያሳክክ የሰውነት ቆዳን በጣት ወይም በጥፍር ወጋ። 4. ለምርጫ፥ ለውድድር በእጩነት አቀረበ።

**ጠቋሚ** ስ 1. አመልካች፥ አንድን ሁኔታ የሚያሳይ። 2. የሚመራ፥ የሚያሳይ (አቅጣጫን)። 3. ሊመረጥ ወይም ሊወዳደር ይገባል ብሎ የሚያምንበትን ሰው በእጩነት የሚያቀርብ።

**ጥቆማ** ስ 1. በሚስጢር፥ በድብቅ መንገር። *ነገሩ በጥቆማ ተደርሶበታል።* 2. ለምርጫ ወይም ለውድድር እጩን የማቅረብ ሂደት።

**ተጠቆመ** ግ 1. በሚስጢር ተነገረ። 2. ለምርጫ ወይም ለውድድር ቀረበ።

**ተጠቋሚ** ስ ለምርጫ ወይም ለውድድር የቀረበ፥ እጩ።

**ተጠቋቆመ** ግ ተጢቃቀሰ።

**ጠቆረ** ግ 1. ከሰል ወይም ጥላሸት መሰለ። 2. ደመና ያዘ፥ ዝናብ አረገዘ (ሰማይ)። 3. ፊልሙ ላይ የተቀረፀው የፎቶግራፍ ምስል እንዲታይ ሆነ ወይም ተደረገ። 4. ክጉዳት፥ ከብስጭት፥ ከፀሃይ ሃሩር፥... የተነሳ መልኩ ጠየመ፥ ከሰል መሰለ።

**ጠቋራ** ቅ በጣም ጥቁር፥ ከሰል የመሰለ።

**ጥቁራት** ስ ንቅሳት፥ ውቅራት።

**ጥቁሬ ዝንጀሮ** ስ ጠቆር ያለ መልክ ያለው የዝንጀሮ አይነት።

**ጥቁር** (ብ.ቁ **ጥቋቁር**) ቅ 1. የከሰል መልክ ያለው። 2. የነጭ ቀለም ተቃራኒ፥ ከሰል ወይም ጥላሸት የመሰለ የቀለም አይነት። 3. ጠይም ወይም ጥቁር ቆዳ ያለው ህዝብ ዘር የሆነ (ሰው)።

**ጥቁር ውሻ ውለድ** (እር.) ጉድ ውለድ።

**ጥቁር መጣፍጥ** ስ ጥቁር አዝሙድ።

**ጥቁር ምላስ** ቅ እርግማኑ ይደርሳል ተብሎ የሚፈራ (ሰው)።

**ጥቁር ራስ** ስ ያልመነኮሰ፥ ቆብ ያልጫነ፥ አለማዊ የሆነ ሰው።

**ጥቁር ሰሌዳ** ስ በጠመኔ እየተጻፈበት ለማስተማሪያ እንዲያገለግል፥ ብዙውን ጊዜ ጥቁር ቀለም ተቀብቶ የተዘጋጀ ሰሌዳ።

**ጥቁር ሰማይ** ስ ደመና የሌለበት የጠራ ሰማይ።

**ጥቁር ሰማያዊ** ቅ 1. ደማቅ ጠቆር ያለ ሰማያዊ መልክ ያለው። ስ 2. ጠቆር ያለ ሰማያዊ ቀለም።

**ጥቁር ስንዴ** ስ ፍሬው ጠቆር የሚል የስንዴ አይነት።

**ጥቁር አዝሙድ** ስ ለዳቦ፥ ለወጥ ማጣፈጫ የሚያገለግል ፍሬው ጥቁር የሆነ ቅመም።

**ጥቁር እንግዳ** ስ 1. መጥቶ የማያውቅ፥ ከፍተኛ ክብርና መስተንግዶ የሚደረግለት ሰው። 2. የጉንዳን የምስጢር ስም።

**ጥቁር እንጨት** ስ ውስጡ ድፍንና በጣም ጠንካራ የሆነ የእንጨት አይነት፥ ዞጲ።

**ጥቁር ደመና** ስ በሰማይ ላይ ጨለማ መስሎ የሚታይ ዝናብ ያዘለ ደመና።

**ጥቁር ድንጋይ** ስ ጠንካራ የሆነ፥ በቀላሉ የማይሰበር፥የማይፈረካከስ የድንጋይ አይነት።

**ጥቁር ገበያ** ስ ህገወጥ የሆነ ግብይት፥ በተለይም የውጭ ምንዛሪ ልውውጥ።

**ጥቁር ገብስ** ስ ፍሬው ጠቆር የሚል የገብስ አይነት።

**ጥቁር ጤፍ** ስ ከሌላው ጤፍ ይልቅ በብረት ማእድን የበለፀገና፥ እንጀራው ሲጋገር ቡናማ መልክ የሚይዝ የጤፍ አይነት።

**ተጠቆረ** ግ 1. ተነቀሰ፥ ተወቀረ። 2. በአመድ ታሸ (ዘንጋዳ)።

**አጠቆረ** ግ 1. መልክን አጠየመ (ሃሩር፥...)። 2. በአመድ አሸ (ዘንጋዳን)። 3. በምርጫ ፈተና ጊዜ ከተሰጡት የመልስ ምርጫዎች መካከል፥ መልሱን በመምረጥ በተሰጠው ተራ ቁጥር ወይም ፊደል ስር ባለው የመልስ ቦታ ላይ ምልክት አደረገ፥ ቀባ። 4. ፎቶግራፍ በፊልም ላይ እንዲታይ አደረገ (ፊልሙን በተለያየ የፎቶግራፍ ቅመሞች ውስጥ በመጨመር)።

**አስጠቆረ** ግ ፊልሙ ላይ ፎቶው ወይም ምስሉ እንዲታይ አደረገ።

**ጠቋሚ** "ጠቆመ" ስር ተመ.

**ጠቋራ** "ጠቆረ" ስር ተመ.

**ጠበለተኛ** "ፀበል" ስር "ፀበለተኛ"ን ተመ.

**ጠበል** "ፀበል"ን ተመ.

**ጠበል ጣዲቅ** "ፀበል" ስር "ፀበል ፀዲቅ"ን ተመ.

**ጠበረረ** ግ 1. በጣም ጋለ፥ ሰማ (ምጣድ) ። 2. ሞቀ፥ ጠራራ ሆነ (ፀሃይ)። 3. ደረቀ፥ ተቃጠለ (ተክል፥ ቅጠል)።

**አጠበረረ** ግ 1. አጋለ፥ አሰማ (ምጣድን)። 2. አደረቀ።

***ጠበረረ**

**ጠብራራ (ጥብርር)** ቅ ቀብራራ፥ ኩሩ፥ ጀግን።

**ጥብርር አለ** ግ ቅብርር አለ፥ ኩራ፥ ታበየ።

**ተንጠባረረ** ግ ኩራ፥ ተንቀባረረ፥ ተጀነነ።

**አንጠባረረ** ግ አንቀባረረ፥ አኩራ፥ ጀነነ።

***ጠበረበረ**

**ተጥበረበረ** ግ ተብረቀረቀ፥ተብለጨለጨ፥ ተንፀባረቀ።

**አጥበረበ (አጭበረበረ)** ግ አንፀባረቀ፥ አብረቀረቀ፥አብለጨለጨ፥ አይን እንዳያይ አደረገ (ነፀብራቅ፥ ብልጭልጭታ)።

**ጠበሰ** ግ 1. ዘይት፥ ቅቤ፥... ጨምሮ በእሳትአንጨረጨረ፥ አበሰለ (ስጋን፥አትክልትን)። 2. ለበለበ፥አቃጠለ፥ተኩሰ።3.መታ (በጥይት፥ በአርጩሜ፥...)። 4. (ዘይ.) አቃጠለ፥ አናደደ፥ አሳረረ። *በነገር ጠበሰኝ።* 5. (ያራዳ አነ.) ሴትን አሽኮረመመ፥ አባበለ።

***መጥበሻ*** ስ እጀታ ያለው ሆኖ ከብረት ወይም ከሸክላ የሚሰራና ለስጋ፥ ለድንች፥... መጥበሻነት የሚያገለግል እቃ።

**ጠባሳ** ቅ 1. በቃጠሎ፥ በቁስለት ምክንያት ሰውነቱ ላይ ምልክት ያለበት። ስ 2. በእሳት ተቃጥሎ ወይም በሌላ ምክንያት ቆስሎ ከዳነ በሂላ በሰውነት ላይ የሚቀረው ምልክት። 3. (ዘይ.) የመጥፎ ድርጊት አሻራ።

**ጠባሳው የማይሽር** የማይረሳ፥ ሁሌም የሚከነክን ።

**ጥብስ** ቅ 1. ያለ ውሃ በዘይት፥ በቅቤ ወይም በእሳት ብቻ የበሰለ (ምግብ)። ስ 2. በዘይት፥ በቅቤ ወይም በእሳት ብቻ የበሰለ ስጋ ።

**ጥብስ ወጥ** ስ ስጋው ለብቻ ከተጠበሰ በሂላ የሚሰራ ወጥ።

**ተጠበሰ** ግ ተቃጠለ፥ ተናደደ፥ አረረ (በነገር)።

**ተጣበሰ** ግ (ያራዳ አነ.) አንድ ነገር ለማግኘት፥ ለማከናወን፥ ጉዳይ ለማስፈፀም ታገለ፥ ተሯሯጠ ወይም በሌላ ሰው አማካይነት አለዚያም በራሱ ቅልጥፍና አንድን ጉዳይ ለማስፈፀም ቻለ።

**ጠበሰቀ** ግ መታ፥ ነረተ (በዱላ፥ በቡጢ)።

**ጠበቀ**[1] ግ 1. አዋለ፥ አገደ (ከብትን)። 2.ተንከባከበ፤ እያየ፥ እየተከታተለ መጥፎ ነገር እንዳይመጣ ጥንቃቄ አደረገ፤ አደጋ እንዳይደርስ ተቆጣጠረ። 3.ቆየ። *ተራ እስከሚደርስህ ጠብቅ።* 4. አከበረ (ህግን፥ መብትን፥..)።

**ጠባቂ** ስ 1. አደጋ እንዳይደርስ ጥንቃቄ ወይም እንክብካቤ የሚያደርግ (በሰው፥ በንብረት ላይ)። 2. ከብት የሚያግድ፤ እረኛ።

**ጥበቃ** ስ ጉዳት ወይም አደጋ እንዳይደርስ ጥንቃቄ የማድረግ፥ የመከታተል ተግባር።

**ጥበቃ ጓድ** ስ የአንድን አካባቢ፥ ፀጥታ ወይም ስነ ስርአት ለማስከበር የተመደበ ሰው፥ ቡድን።

**ጥብቅ** ቅ እንዳታረግዝ የግብረስጋ ግንኙነት ከማድረግ የተቆጠበች (ሴት)።

**ተጠበቀ** ግ 1. በጥንቃቄ፥ በእንክብካቤ ተያዘ። 2. እንዳለ ሆነ፥ ፀና። 3. ተከበረ፥ ተግባራዊ ተደረገ (ህግ፥ ደንብ)። 4. ተከለከለ፥ተቆጠበ፥ ተወገደ፥ ተገለለ።*ከመጠጥ ተጠብቆ ይኖራል።*

**አስጠበቀ** ግ እንዲጠብቅ፥ እንዲከበር አደረገ። *መብቱን አስጠበቀ።*

**ጠበቀ**[2] ግ ጠነከረ፥ ጠና፥ ከረረ፥ በቀላሉ የማይፈታ ሆነ።

**የጠበቀ ሰላምታ** የጋለ፥ ከፍ ያለ ሰላምታ።

**የጠበቀ ግንኙነት** የቀረበ ግንኙነት፥ ወዳጅነት።

**ጠባቃ** ቅ1. ጠንካራ፥ ልል ያልሆነ። 2. ጠባብ።

**ጥብቅ** ቅ 1. ጠንካራ፥ የከረረ፥ በቀላሉ የማይነቃነቅ፥ የማይፈታ። 2. ዋና፥ ብርቱ። *ለጥብቅ ጉዳይ ትፈለጋለህ/ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ።* 3. የቅርብ፥ ታማኝ። *እገሌ ጥብቅ ወዳጄ ነው።* 4. ጠንቃቃ። 5. (ዘይ.)ንፉግ፥ ስስታም።

**አጠበቀ** ግ 1. አጠነከረ፥ እንዳይላላ፥ በቀላሉ እንዳይፈታ አደረገ። 2. አልተው አለ፥ አከረረ (ሃዘንን፥ ነገርን)።

**አጥባቂ** ቅ ሁኔታዎችን በቀላሉ የማያይ፤ አክራሪ።

**አጥብቆ** ተው.ግ 1. በጣም። *ነገር አጥብቆ ይሸሻል።* 2.አጠንክሮ፥ ደጋግሞ።*ለለስውየው አጥብቆ ጠየቀኝ።*

**ጠበቀ**[3] ግ 1. ቆየ። *እስኪመጣ ጠብቀው።*2. ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል ብሎ ገመተ፥ አሰበ (አንድ ነገር)። 3. አንድ ነገር እስከሚሆን ታግሶ ቆየ።

**ተጠበቀ** ግ ይሆናል ተብሎ ተገመተ። *የተጠበቀውን ያህል ውጤት አገኘተናል።*

**ተጠባበቀ** ግ 1. ጠበቀ። 2. ተከታተለ፥ በአይነ ቁራኛ ተመለከተ።

***መጠባበቂያ*** ስ 1.ለችግር፥ ለአደጋ፥... ጊዜ የተቀመጠ ገንዘብ። 2. በጎደለ፥ በተበላሸ ነገር ፋንታ በምትኩ የሚገባ እቃ።

**ተጠባባቂ** ቅ 1. ምትክ፥ በጎደለው ፋንታ የሚተካ፥ የሚገባ። ስ 2. ሹመቱ ወይም የተሰጠው የሃላፊነት ቦታ ገና ያልፀደቀለት ወይም ለጊዜው ብቻ ሃላፊ ሆኖ እንዲሰራ የተመደበ። 3. በአንድ የውድድር ጨዋታ ወቅት የተመደበው ተጫዋች ቢጎዳ ወይም በሌላ ችግር መጫወት ባይችል በጎደለው እንዲተካ የሚመደብ ተጫዋች።

***ጠበቀ[1]**

**መጣብቅ** ስ ማጣበቂያ::

**ጣብቂያ** ስ 1. ጠባብ የሆነ መተላለፊያ ቦታ:: 2. ጭንና ጭን የሚነካካበት ቦታ:: 3. (ዘይ.) አስቸጋሪ፥ አስጨናቂ ሁኔታ::

**ተጣበቀ** ግ 1. ተያያዘ፥ ተላከከ፥ ተለጠፈ (በሙጫ፥ በሙቅ፥...):: 2. በሁለት ነገሮች መካከል ገብቶ ተጨቆነ፥ ታፈነ፥ ተጨነቀ::3. ልክክ፥ ልጥፍ አለ::

**አጣበቀ** ግ 1. ላከከ፥ ለጠፈ፥ አያያዘ (በሙጫ፥ በሙቅ፥...):: 2.ያዘ (ሙጫው፥ ማጣበቂያው):: 3. በመካከል አስገብቶ አፈነ፥ አስጨነቀ:: 4. ጠበበ፥ አልበቃ አለ (ልብስ፥ ጫማ)::

**ማጣበቂያ** ስ እንደሙጫ፥ ሙቅ ያለ የተለያዩ ነገሮችን ለማያያዝ ወይም ለመለጠፍ የሚያገለግል ነገር::

**አጣብቂኝ** ስ 1. ሰውነትን የሚያጣብቅ፥ ሰፊ ያልሆነ ልብስ:: 2. በጣም አስጨናቂ፥ አስቸጋሪ ሁኔታ:: 2. በሁለት ድንጋዮች መካከል የሚገኝ እጅግ በጣም ጠባብ የሆነ መተላለፊያ::

***ጠበቀ[2]**

**ጠበቃ** ስ ባለጉዳይን ወክሎ በፍርድ ቤት የሚከራከር፥ የሚሟገት፤ ነገረ ፈጅ፤ አቡካቶ:: የህግ ጠበቃም ይባላል::

**ከጠበቃዬ** ጠበቃዬ ይናገርልኝ፥ ይሟገትልኝ ለማለት የሚነገር አባባል::

**ጠበቃ ወለደ** ለጉዳዩ የሚከራከርለትን ሰው አቆመ ወይም ወከለ::

**ጠበቃ ገዛ** ለጉዳዩ በፍርድ ቤት የሚከራከርለትን ጠበቃ አቆመ (ገንዘብ ከፍሎ)::

**ጥብቅና** ስ ሌላን ሰው ወክሎ የመሟገት፥ የመከራከር ተግባር::

**ጥብቅና ቆመ** ስ ሌላውን ሰው ወክሎ ተሟገተ፥ በፍርድ ቤት ተከራከረ::

**ጠበበ** ግ 1. አልበቃ አለ፥ አነሰ (ለምሳሌ ልብስ):: 2. ስፋት አጣ፥ አነሰ (ቦታ፥ መሬት፥..):: 3. ትንሽ ሆነ፥ አነሰ:: *እድሉ እየጠበበ መጣ::*

**ጠባብ** ቅ1. ስፋት የሌለው:: *ጠባብ ድልድይ/ጠባብ ክፍል::* 2. በልክ ያልተሰራ፥ በቂ ያልሆነ:: *ጠባብ ልብስ::* 3. ውሱን የሆነ፥ አነስተኛ:: *አዲስ ሰራተኛ ለመቅጠር ያለው እድል በጣም ጠባብ ነው::* 4.የተጠጋጋ፥ የተቀራረበ:: *ውድድሩን ያሸነፉት በጠባብ የነጥብ ልዩነት ነው::*

**ጠባብ ብሄረተኛ** ቅ ለጎሳው ብቻ የሚያስብና የሚያደላ፥ በሌላው ላይ ጥላቻ የሚያሳይ::

**ጠባብ ብሄረተኝነት** ስ የጠባብ ብሄረተኛ አቋምን የያዘ አመለካከት::

**ጠባብ አስተሳሰብ (አመለካከት)** ጥልቀት የሌላው፥ በስፋት የማይገነዘብ አርቆ ማየት የጎደለው::

**ጥበት** ስ ሰፊ ያለመሆን፥ መጥበብ፥ የስፍራ ወይም የቦታ ማነስ::

**ተጣበበ** ግ ተጨናነቀ፥ ተፋፈገ::

**አጠበበ** ግ 1. ስፋቱን ቀነሰ፥ አሳነሰ፥ ጠባብ አደረገ:: 2. ያለመጠኑ አሳንሶ ሰራ ወይም ሰፋ (ልብስን፥ ጫማን)::

**አጣበበ** ግ 1.አጨናነቀ፥ መፈናፈኛ ቦታ አሳጣ:: 2.ስፍራን ወይም ቦታን ሞላ፥ ያዘ:: *ገበያውን ያጣበበው የኮንትሮባንድ እቃ ነው::*

***ጠበበ**

**ጠቢብ** ቅ ብልህ፥ አዋቂ::

**ጥበብ** ስ 1. ብልሃት፥ እውቀት፥ ዘዴ:: 2. በተለያየ ዲዛይንና ቀለም የሚሰራ የሃበሻ ልብስ ጥለት::

**በጥበብ** ተው.ግ. በዘዴ፥ በብልሃት::

**ጥበበኛ** ቅ አዋቂ፥ ብልሃተኛ፥ ዘዴ የሚያውቅ::

**ተጠበበ** ግ ( በፍልስፍና፥ በእውቀት፥..) ተራቀቀ፥ ተፈላሰፈ::

**ጠበንጃ "ጠመንጃ"** ን ተመ.

**ጠበኛ "ጠብ"** ስር ተመ.

**ጠበደለ** ግ ወፈረ፥ወደለ::

**ጠብደል** ቅ ወፍራም፥ ወደል::

**አጠበደለ** ግ በጣም አወፈረ፥ አወደለ::

**ጠበጠበ** ግ 1. ገረፈ፥ ሸነቆጠ:: 2. በቀስታ መታ መታ አደረገ::

**ጥብጠባ** ስ (ክር.) በክርስቶስ ላይ የተፈፀመውን ግርፋት ለማሰብና የስቃዩ ተካፋይ የመሆንን እምነት በምሳሌ ለማመልከት፥ የስቅለት በአል በሚከበርበት እለት ቀሳውስት የምእመናኑን ጀርባ በወይራ ዝንጣፊ በቀስታ መታ መታ በማድረግ እያንዳንዱ ምእመን ምን ያህል መስገድ እንዳለበት ትእዛዝ የሚሰጡበት ስርአት::

**ጥብጥባት** ስ የግርፋት ምልክት፥ ሰንበር::

**ጠቢብ "*ጠበበ"** ስር ተመ.

**ጠባ[1]** ግ መገመገ፥ መጠመጠ(ጡትን)::

**አጠባ** ግ ጡጦ በመስጠት መገበ::

**አጠባች** ጡት በመስጠት መገበች::

**አጥቢ እንስሳት** ስ ልጆቻቸውን ጡት በማጥባት የሚያሳድጉ እንስሳት::

**ጠባ[2]** ግ 1. ነጋ፥ ብርሃን ሆነ፥ ወገግ አለ

(ሌሊቱ+ ጨለማው):: 2. ገባ+ ባተ:: *መስከረም ጠባ::*

**ጥቢ** ስ ክረምት አልፎ መስከረም እንደገባ ያለው ጊዜ::

**ጥባት** ስ ንጋት::

**አጥቢያ** ስ ንጋት::

**አጥቢያ ኮከብ** ስ ንጋት ላይ ጎላ ብሎ የሚታይ ኮከብ::

**ጠባ**[3] ግ አረደ+ ብልት አወጣ (ለምሳሌ ፍየልን)::

**ጠባሳ "ጠበሰ"** ስር ተመ.

**ጠባቂ "ጠበቀ**[1]**"** ስር ተመ.

**ጠባቃ "ጠበቀ**[2]**"** ስር ተመ.

**ጠባብ "ጠበበ"** ስር ተመ.

**ጠባይ** ስ 1. አመል+ ባህርይ:: 2. አንድ እቃ÷ መሳሪያ ወይም መኪና በትክክል የሚሰራበት ሁኔታ+ ዘዴ:: *የመኪናዋን ጠባይ ያውቀዋል::* 3. ሁናቴ:: *የአየር ጠባይ::*

**ጠባዩ ተለወጠ** 1. ጠባዩ ተበላሸ:: 2. በፊት የነበረውን ጠባይ ቀየረ::

**የጠባይ ጉድለት** የጠባይ ብልሹነት::

**ጠብ** ስ ጥል÷ አምባጓሮ::

**ጠብ አበቀለ /አነሳ** ተጣላ÷ ጥል ጀመረ::

**ጠብ ጫረ** ነገር ቆሰቆሰ ÷ ተነኮሰ::

**ጠበኛ** ቅ 1. ጥለኛ÷ ባላጋራ÷ ባላንጣ:: *ከሰውየው ጋር ጠበኛ ነኝ::* 2.ጠብ ወይም አምባጓሮ የሚወድ÷ ነገረኛ::

**ጠብ**

**ጠብታ** ስ በአንድ ጊዜ ጠብ የሚል የተወሰነ መጠን ያለው ፈሳሽ (የመድሃኒት ወይም የሌላ ነገር)::

**ጠብ አለ** ግ መሬት+ እቃ÷... ላይ ወደቀ÷ አረፈ (የፈሳሽ ነጠብጣብ ወይም ሌላ ነገር)::

**ጠብ አይለውም** ስስታም+ ጩቅ ነው::

**ጠብ አይልም** አይጠራቀምም:: *የዛሬው ስራ ጠብ አይልም::*

**ጠብ አደረገ** ግ በትንሹ ጣለ÷ አፈሰሰ÷ አወረደ:: 2. ገደለ:: *ወባ ጠብ አደረገው::*

**ጠብ እርግፍ አለ** በደስታ ተቀበለ÷ አስተናገደ+ ተሽቆጠቆጠ::

**ጠብ እርግፍ አድርጎ ተወ** ፈፅሞ÷ ጨርሶ ተወ::

**ጠብ ጠብ አለ** ግ ተንጠባጠበ::

**ጠብ ጠብ አደረገ** ግ አንጠባጠበ::

**ተንጠባጠበ** ግ ቀስ እያለ በትንሽ በትንሹ ወረደ+ ፈሰሰ:: 2.ቀስ እያለ መጣ+ ተገኘ:: *ሰው እየተንጠባጠበ መጣ::*

**አንጠባጠበ** ግ 1. በትንሽ በትንሹ አፈሰሰ÷ አወረደ÷ ጣለ:: 2. አልፎ አልፎ አወረደ÷ ወረወረ÷ ጣለ:: 3. በየቦታው አዝረከረከ÷ በተነ::

**ጠብራራ "*ጠበረረ"** ስር ተመ.

**ጠብታ "ጠብ"** ስር ተመ.

**ጠብደል "ጠበደለ"** ስር ተመ.

**ጠቦት** ስ ጡት መጥባት ያቋረጠና ከወጠጤ አነስ ያለ የበግ ወይም የፍየል ግልገል::

**ጠነሰሰ** ግ 1. ጠላ ለመጥመቅ÷ አረቄ ለማውጣት÷... ብቅልና ጌሾን በጠበጠ÷ አዋሃደ:: 2. ወጠነ÷ አዘጋጀ (ደባን÷ ተንኮልን÷...)::

**ጠንሳሽ** ቅ አቀናባሪ÷ ጀማሪ÷ ወጣኝ (ሴራን÷ አድማን...)::

**ጥንስስ** ስ 1. የጠላ ጠመቃ ጅምር (የጌሾና የብቅል ብጥብጥ):: 2. የአንድ ነገር ወይም ተንኮል ውጥን÷ እቅድ::

**ጥንስስ መሰለ** ዳመና መሰለ÷ ጠቆረ::

**ተጠነሰሰ** ግ ታቀደ÷ ተወጠነ÷ ተቀነባበረ (ሴራ÷ ተንኮል÷...)::

**ጠነቀለ** ግ በጥቂቱ ወይም በትንሹ ቆነጠረ (ቅቤን÷ ማርን÷...)::

***ጠነቀረ**

**ጥንቅር** ስ ጥርቅም÷ ስብስብ::

**ተጠናቀረ** ግ ተጠራቀመ÷ ተሰበሰበ::

**አጠናቀረ** ግ አጠራቀመ÷ ሰበሰበ::

**ጠነቀቀ** ግ እንዳይበላሽ÷ ውጤቱ መጥፎ እንዳይሆን÷... ጥንቃቄ አደረገ:: *ስራህን ጠንቅቀህ ስራ::*

**ጠንቅቆ ያውቃል** ሙሉ በሙሉ ወይም በደንብ አድርጎ ያውቃል::

**ጠንቃቃ (ጥንቁቅ)** ቅ ዝርክርክ ያልሆነ÷ ብልህ÷ አስተዋይ÷ ልባም::

**ጥንቃቄ** ስ አንድ መጥፎ ነገር ከመፈፀሙ ወይም ከመድረሱ በፊት ወይም ብልሽት÷ ስህተት÷ ችግር+... እንዳይፈጠር ለመከላከል የሚደረግ ትኩረት+ ዝግጅት÷ እንክብካቤ::

**ጠንቀቅ አለ** ግ ተጠነቀቀ::

**ተጠነቀቀ** ግ 1. ተዘጋጀ (መጥፎ ሁኔታን ለመከላከል):: 2. አደጋ÷ ክፉ ነገር÷ ብልሽት÷... እንዳይደርስ ጥንቃቄ አደረገ::

**ተጠናቀቀ** ግ ተፈፀመ÷ ተከናወነ÷ ተሰርቶ አለቀ:: *ሊግናሩ ትናንት ተጠናቀቀ::*

**አጠናቀቀ** ግ አከናወነ÷ ፈፀመ÷ ጨረሰ::

**አስጠነቀቀ** ግ 1. አስገነዘበ÷ ማሳሰቢያ ሰጠ:: 2. ጥንቃቄ እንዲደረግ አዘዘ::

**ማስጠንቀቂያ** ስ 1. አንድ ነገር መደረግ

እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ለማሳወቅ በፅሁፍ ወይም በቃል የሚሰጥ ማስገንዘቢያ+ ትእዛዝ:: 2. ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚሰጥ ምልክት::

**በማስጠንቀቂያ ታለፈ** ጥፋቱን ሌላ ጊዜ ቢደግም መጥፎ ሁኔታ ወይም ቅጣት ሊከተል እንደሚችል ተገልፆለት ለጊዜው ይቅርታ ተደረገለት::

**ጠነቆለ**[1] ፡ በአስማት+ በጥንቆላ ይህ ይሆናል ብሎ ተነበየ+ ተናገረ::

**ጠንቋይ** ስ በአስማት ወይም ዛጎል+ ጠጠር በመጣል ይህ ይሆናል ብሎ የሚናገር+ የሚተነብይ፤ እንዲሁም በአስማት+ በመተት አማካይነት የተለያዩ አስገራሚ ድርጊቶችን የሚፈፅም ነው ተብሎ የሚነገርለት ሰው::

**ጥንቆላ** ስ ወደፊት እንዲህ ይሆናል ወይም ይጀረጋል ብሎ የመናገርና እንዲሁም በአስማት ወይም በድግምት+... አማካይነት የተለያዩ አስገራሚ ድርጊቶችን የመፈፀም ተግባር::

**አስጠነቆለ** ግ ኮከብ አስቆጠረ፤ ስለ እድሉ ወይም ስለሚያጋጥመው ሁኔታ ለማወቅ ወይም መልካም ነገር እንዲያጋጥመው ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ጠየቀ+ አስጠየቀ::

**ጠነቆለ**[2] ግ ወጋ+ ደነቆለ:: *እንጨት ላይ እንጨት ጠነቆለኝ::*

***ጠነበረ**

**ጠንባራ** ቅ (ስድብ) እውር+ ደንባራ::

**ጠንባራ ሽሮ** (የን. አነ.) ቅባት የሌለውና በጥሩ ሁኔታ ያልተሰራ የሽሮ ወጥ::

**ተጠናበረ** ግ ተደናበረ::

**አጠናበረ** ግ 1.አደናበረ:: 2. በጥፊ መታ+ አጮለ+ አጠናገረ::

**ጠነበሰ** ግ በጥፊ መታ+ አጮለ::

**ጠንባሳ** ቅ (ስድብ) ጨንባሳ+ ደንባራ::

**አጠናበሰ** ግ 1. አጨናበሰ+ አደናበረ:: 2. በጥፊ መታ+ አጮለ::

**ጠነበዘ** ግ 1. በጣም ሰከረ:: 2. ታወረ+ ደንባዛ ሆነ::

**ጠንባዛ** ቅ (ስድብ) 1. ደንባዛ+ ሰክሮ የሚደናበር:: 2. አይኑ የማያይ ::

**ጥንብዝ አለ** ግ በጣም ሰከረ::

**ጠነባ** ግ ገማ+ ሸተተ::

**ጥንብ (ጥምብ)** ቅ 1. የበሰበሰ+ የገማ:: 2. (ስድብ) ቆሻሻ+ ግማታም::

**ጥንቡን ጣለ** ረከሰ፤ የሚፈልገው ወይም የሚገዛው አጣ::

**ጥንብ አንሳ** ስ የሞተ እንስሳን ስጋ የሚበላ አሞራ፤ጆፌ አሞራ::

**ጥንባት** ስ መጥፎ ሽታ+ ግማት::

**አጠነባ** ስ አገማ+ መጥፎ መጥፎ እንዲሸት አደረገ::

**ጠነነ** ግ 1. ዘንበል አለ+ አገደደ:: 2. ጠመመ+ ከፋ:: 3. ከበደ+ አዋኪ ሆነ+ አቃተ:: *ትምህርቱ ጠነነኝ::*

**ጠናና** ቅ 1. ዘንበል ያለ+ገዳዳ:: 2. ጠማማ+ ክፉ::

**አጠነነ** ግ 1. አዘነበለ+ አገደደ:: 2. ከፋ+ ጠመመ+ ለገመ:: 3. አከበደ፤ አዋኪ ወይም አስቸጋሪ አደረገ::

**ጠነከረ** ግ 1. በረታ+ ጎበዘ:: *ትምህርትህን ጠንክረህ ተማር::* 2. ጠና:: *ሕጻኑ ጠንክሯል::* 3. አየለ:: *ጠላት እየጠነከረ መጣ* :: 4. ጠጠረ+ ከረረ:: 5. ከበደ+ አስቸጋሪ ሆነ::

**ጠንካራ** ቅ 1. ብርቱ+ ጎበዝ:: *በችግር የማይፈታ ጠንካራ ሰው::* 2. ጠጣር+ ከራራ+ ጠባቃ::3.ብቀላሉ የማይበላሽ+ የማይሰበር+... ጥሩ (እቃ+...)::

**ጥንካሬ** ስ ብርታት:: 2. ጥብቀት፤ አቅም::

**ተጠናከረ** ግ 1. ተበረታታ+ ጎበዘ:: 2. ሃይሉ ጨመረ ወይም ከበፊቱ የተሻለ ወይም የበለጠ እንዲሆን ተደረገ::

**አጠነከረ** ግ 1. አበረታ+ ሃይል ሰጠ:: 2. አስቸጋሪ አደረገ::

**አጠናከረ** ግ ሃይል ጨመረ ወይም ከበፊቱ የበለጠ እንዲሆን አደረገ፡፡

**ማጠናከሪያ** ቅ ቀደም ሲል በነበረው ላይ እየተጨመረ የነበረውን የበለጠ የሚያሻሽል+ የሚያሰፋ:: *የማጠናከሪያ ትምህርት/ የማጠናከሪያ ሳዋጅ::*

**ጠነዛ** ግ 1.እሳት ስለአነሰው በደንብ ሳይበስል ቀረ:: 2.አረጀ+ ገረጀፈ:: 3. (ዘይ.) ተሰለቸ+ እጅ እጅ አለ::

**ጠናዛ** ቅ (ስድብ) ያረጀ+ የሸመገለ+ የገረጀፈ::

**አጠነዛ** ግ በደንብ ሳያበስል ቀረ::

***ጠነገ**

**ጥንግ** ስ ከጠፍር ተጠርዞ የተሰራ ሩር::

**አጠነጋ** ግ 1. በጥፊ+ በዱላ+... መታ:: 2. ቀላ+ ለጋ (ጥንግን)::

***ጠነገረ**

**ጠንጋራ** ቅ 1. ሸውራራ+ አይኖቹ በየፊናቸው ወደ ተለያየ አቅጣጫ የሚመለከቱ የሚመስል:: 2. እውር::

**ተጠናገረ** ግ 1. ተንሸዋረረ:: 2. ታወረ::

**አጠናገረ** ግ 1. አንሸዋረረ:: 2. እውር አደረገ:: 3. በጥፊ መታ+ አጠናፈረ::

**ጠነጠነ**[1] ግ አረጀ፥ ሸመገለ።

**ጥንጣን** ስ 1. እንጨት የሚበላ የትል አይነት፥ ቁንቁን፥ ነቀዝ።2. ነቀዝ ወይም ቁንቁን ከበላው እንጨት የሚወጣ ዱቄት መሰል ነገር።

**ጥንጣን ሆነ** በጣም ደቀቀ፥ ዱቄት ሆነ።

**ጠነጠነ**[2] ግ 1. መታ፥ ደበደበ። 2. ወረወረ፥ በተነ። *ሃብቱን ጠነጠነው።*

***ጠነጠነ**

**ጥንጥን** ስ ልቃቂት፥ ድውር።

**አጠነጠነ** ግ 1. አዳወረ። 2.ጠመጠመ፥ ጠቀለለ (ለምሳሌ ፈትልን)። 3.(ዘይ.) ተበተበ፥ ሸረበ (ነገርን)። *ነገር ማጠንጠን ይወዳል።*

**ጠነፈፈ** ግ ጠፈፍ ወይም መጠጥ አለ።

**ጥንፊት** ቅ 1. ከንፍሮ፥ ከአሹቅ፥... ላይ የሚወገደውና ሲጠነፈፍ የሚወጣው ፈሳሽ ።2. እላቂ፥ ሙጣጭ፥ ጭላጭ (የፈሳሽ)።

**አጠነፈፈ** ግ 1. አንጠፈጠፈ፥ አፈሰሰ፥ አስወገደ (ለምሳሌ ውሃን ከንፍሮ ውስጥ)። 2. ጨረሰ፥ አሟጠጠ።

**ማጠንፈፊያ** ስ ፈሳሽን ለብቻው (ከንፍሮ፥ ከፓስታ፥...) ለይቶ ለማፍሰስ ወይም ለማጥለል የሚያስችል እቃ፥ ወንጠፍት።

**ጠና** ግ ጠነከረ፥ በረታ።

**መጥኔ ይስጥህ** ብርታቱን፥ ጥናቱን ይስጥህ ለማለት የሚነገር አባባል።

**በጠና** በሃይል፥ በብርቱ። *በጠና ታሟል።*

**ፅኑ (ጥኑ)** ቅ 1. ብርቱ፥ ጠንካራ። 2. ከባድ፥ ከፍተኛ። *ፅኑ ረሃብ።*

**ፅኑ እስራት** ስ ከሌሎች እስረኞች ይበልጥ እስራቱ የሚከብድበት የእስራት አይነት።

**ፅናት(ጥናት)** ስ ጥንካሬ፥ ብርታት፥ ችግርን መከራን የመቋቋም ችሎታ።

**ጠና አለ** ግ ጠነከረ፥ በረታ።

**ጠና ያለ** ቅ በሰል ያለ፥ በጣም ያላረጀ (ለሰው)።

**ተፅናና** ግ ተበረታታ፥ ተረጋጋ (ከሃዘን)።

**አፅናና (አጥናና)** ግ አረጋጋ፥ አበረታታ።

**ማፅናኛ (ማጥናኛ)** ስ የሃዘን ማስረሻ።

**አፅናኝ (አጥናኝ)** ቅ አበረታች፥ የሚያበረታታ፥ የሚያረጋጋ።

***ጠና**

**ጥናት** ስ 1. የተማሩትን በመከለስ፥ በማንበብ፥ በመወያየት ጉዳዩን ይበልጥ የመረዳት ሂደት፤ ቅፀላ። 2. ስለአንድ ነገር በይበልጥ ለማወቅ ወይም ለመረዳት የሚደረግ የንባብ ወይም የክለሳ ተግባር። 3. በአንድ ጉዳይ ላይ በማተኮር ስለ ሁኔታው፥ ስለ ችግሩ፥ ስለ መፍትሄው ትንተናና ማጠቃለያ የሚሰጥ የምርምር ተግባር ወይም ውጤት።

**ተጠና** ግ 1. ታወቀ፥ ግልፅ ሆነ፥ ስለምንነቱ ይበልጥ ታወቀ። 2. በምርምር፥ በጥናት ግልፅ ሆነ ወይም ተገመገመ።

**ተጠናና** ግ ጠባይ ለጠባይ ወይም ባህሪ ለባህሪ ተዋወቀ።

**አጠና** ግ 1. የተማረውን በመከለስ ወይም እንደገና በማንበብ ይበልጥ አወቀ፥ ተረዳ፥ ተገነዘበ። 2. ጥናት፥ ምርምር አደረገ።

**አጥኚ** ስ ስለአንድ ነገር ሁኔታና ምንነት መርምሮና አጥንቶ የሚያቀርብ ተመራማሪ።

**አስጠና** ግ ስለአንድ ነገር ጥናት እንዲካሄድ አደረገ።

**ጠናና** "ጠነነ" ስር ተመ.

**ጠናዛ** "ጠነዘ" ስር ተመ.

**ጠኔ** ስ ፅኑ ረሃብ (አቅም የሚያሳጣ፥ የሚጥል)።

**ጠኔያም** ቅ (ስድብ) ረሃብ ያጠቃው፥ ችጋራም።

**ጠንሳሽ** "ጠነሰሰ[1]" ስር ተመ.

**ጠንቀኛ** "ጠንቅ" ስር ተመ.

**ጠንቃቃ** " ጠነቀቀ" ስር ተመ.

**ጠንቅ** ስ 1. የበሽታ ወይም የሌላ መጥፎ ነገር ውጤት። 2. ሰበብ፥ መዘዝ (የበሽታ፥ የመጥፎ ነገር፥...)።

**ጠንቀኛ** ቅ መዘዘኛ፥ መጥፎ ውጤት የሚያስከትል።

**ጠንቋይ** "ጠነቆለ" ስር ተመ.

**ጠንበለል(ጠምበለል)** ስ 1.እንደሃረግ ራሱን ችሎ የማይቆምና ጥሩ መአዛ ያለው የእፅዋት አይነት። 2. (ዘይ.) ለግላጋ (ወጣት)።

**ጠንባራ** "*ጠነበረ" ስር ተመ.

**ጠንባሳ** "ጠነበሰ" ስር ተመ.

**ጠንባዛ** "ጠነበዘ" ስር ተመ.

**ጠንካራ** "ጠነከረ" ስር ተመ.

**ጠንገሎ** "ጠረንገሎ" ን ተመ.

**ጠንፍ** ስ ዳርቻ፥ ጠርዝ።

**ጥንፍ (ፅንፍ)** ዝ.ከ.

**አጥናፍ (አፅናፍ)** ስ ዳርቻ፥ ጠንፍ።

**ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ** ከዳር እስከ ዳር፥ ከጠረፍ እስከ ጠረፍ፥ በመላው ሃገር።

***ጠወለወለ**

**ጥውልውል አደረገ** ግ አጥወለወለ።

**አጥወለወለ** ግ አቅለሸለሸ፥ አዞረ።

**ጠወለገ** ግ 1. ልምላሜ አጣ፥ እንደመድረቅ አለ። 2. ተጎሳቆለ።

**ጠውላጋ** ቅ 1. የጠወለገ፥ እንደ መድረቅ ያለ (ተክል)። 2. (ዘይ.) የተጎሳቆለ፥ ሃይል ያነሰው፥ ደካማ።

**ጠወረ** "ጦረ" ን ተመ.

**ጠዋት** "ጧት" ን ተመ.

**ጠውላጋ** "ጠወለገ" ስር ተመ.

**ጠዘጠዘ** ግ 1. ጠቅ ጠቅ እያደረገ አመመ፥ ነዘረ (ቁስል)። 2. ነደፈ፥ ወጋ፥ ጠቅ አደረገ (ለምሳሌ ንብ፥ ተርብ)። 3. (ዘይ.) ጨቀጨቀ፥ ነተረከ (በነገር፥...)።

**ጥዝጣዜ** ስ እየቆየና ጠቅ ጠቅ እያደረገ የሚያም ወይም የሚነዝር ህመም።

**ተጠዛጠዘ** ግ 1.ተዋጋ፥ ተተጋተገ፥ ተቆናደደ (በጅራፍ፥ በቀስት፥ በጥይት፥...) ። 2. (ዘይ.) በነገር ተነታረከ፥ ተሰዳደበ።

**ጠየመ** ግ መልኩ በጥቁርና በቀይ መካከል ሆነ፥ ደበብ ያለ ቀለም ያዘ።

**ጠይም** (ብ.ቁ . **ጠያይም**) ቅ መልኩ ጥቁር ወይም ቀይ ሳይሆን መሃከለኛ ወይም ደበብ ያለ የሆነ(ሰው)።

**አጠየመ** ግ 1. በፊት ከነበረው ትንሽ ጠቆር አደረገ (መልክን)። 2. (ዘይ.) ፊትን አከፋ (ከጥላቻ የተነሳ)።

**ጠየቀ** ግ 1. የአንድን ሰው ወይም ነገር ምንነትና ማንነት፥ አድራሻ፥... ለመረዳት ወይም ለማወቅ ጥያቄ አቀረበ፥ መልስ ፈለገ። 2. አየ፥ ጎበኘ (በሽተኛን፥ አራስን፥...) ። 3. መረመረ፥ አውጣጣ። 4. አንድ ነገር እንዲደረግለት ወይም እንዲፈፀምለት ፍላጎቱን ነገረ። 5. ለጋብቻ ወይም ለወዳጅነት መፈለጉን ለተፈለገው ሰው ገለፀ። 6. አስፈለገ። *ስራ ለመቀጠር ዲፕሎማ ጠየቀ/ህንፃውን ለመጨረስ ብዙ ገንዘብ ጠየቀ /ለድል ለመብቃት ብዙ መስዋእትነት ጠየቀ።*

**መጠይቅ** ስ ስለ አንድ ነገር መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት አስፈላጊውን መረጃ ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎች ወይም ጥያቄዎቹን የያዘ ቅፅ።

**ልጠየቅ** በእሰጥ አገባ ሙግት ጊዜ ከሳሽ "ተጠየቅ" ሲል ተከሳሽ "ልጠየቅ" በማለት የክሱን ቃል ለመስማት ዝግጁ መሆኑን ይገልፅበት የነበረ አባባል።

**ጠያቂ** ቅ 1. ዘመድን፥ ወዳጅን፥ ህመምተኛን፥... የሚጎበኝ። 2. ጥያቄ አቅራቢ።

**ጠያቂዬ ነው** በየጊዜው የሚጎበኘኝ፥ ችግሬን የማዋየውና የሚረዳኝ ነው።

**ጥያቄ** ስ ስለ አንድ ነገር ለማወቅ፥ ለመረዳት ወይም አንድ ነገር ለማግኘት በመፈለግ በቃል ወይም በፅሁፍ ለሚመለከተው የሚቀርብና መልስ የሚሻ ሃሳብ።

**ጥያቄ አቀረበ** ጠየቀ።

**ተጠየቀ** ግ 1. ጥያቄ ቀረበ ወይም ቀረበለት። 2. ሃላፊነት ውስጥ ገባ ። *በዚህ ውሳኔ እኔ እጠየቅበታለሁ።*

**ተጠየቅ** 1. በእሰጥ አገባ ሙግት ጊዜ ከሳሽ ተከሳሽን "ክሱን ስማና መልስ ስጥ" ለማለት ይናገረው የነበረ ቃል ወይም አባባል። 2. እርስ በርሳቸው የተያያዙና የማይፋለሱ ሃሳቦች ከአንድ መንደርደሪያ ሃሳብ በመመንጨትና ከርሱም ጋር በመያያዝ በተወሰኑ የአስተሳሰብ ህግጋት መሰረት ወደ ትክክለኛ መደምደሚያ የሚያመሩበት ሁኔታ።

**ተጠያቂ** ስ ሃላፊ፥ የጉዳዩ ባለቤት፥ ተጠሪ። 2.በሳል ምሁር፥ ሊቅ (ለሚቀርብለት ትምህርታዊ ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ሊሰጥ የሚችል) ።

**ተጠያየቀ** ግ በተወሰነ ጊዜ እየተገናኘ ሃሳብ ተለዋወጠ፥ ተወያየ፣ ተረዳዳ።

**አጠየቀ** ግ ማስረጃ ሆነ፥ አረጋገጠ። *ትናንት አለመምጣቱ ከሃሳባችን የተለየ መሆኑን ያጠይቃል* (የቆየ አባባል)።

**አጠያየቀ** ግ 1. አፈላለገ፥ እዲፈለግለት አደረገ (የሚሻውን ነገር ለማግኘት)። 2. አጠራጣሪ ሆኖ ተገኘ።

**አጠያያቂ** ቅ በግልፅ ያልታወቀ፥ አጠራጣሪ፥ አወዛጋቢ።

**አስጠየቀ** ግ በሃላፊነት አስከሰሰ፥ አስወነጀለ። *የህዝብን ገንዘብ ያለአግባብ ማባከን በህግ ያስጠይቃል።*

**ጠያፍ** "*ፀየፈ" ስር "ፀያፍ"ን ተመ.

**ጠይም** "ጠየመ" ስር ተመ.

**ጠይብ** ስ 1.በድሮ ስርአት እንደ ሸማኔ፥ አንጠረኛ፥... ያሉትን ባለሙያዎች አንኳስሰው የሚጠሩበት ቃል።2. ቡዳ።

***ጠደፈ**

**ጥድፊያ** ስ ችኮላ፥ ፍጥነት (የስራ፥ የአካሄድ)።

**ተጣደፈ** ግ 1. ተቻኮለ (አንድን ነገር ቶሎ ወይም በፍጥነት ለማድረግ)። 2. በፍጥነት ወይም ቶሎ ቶሎ ተሰራ፥ ተካሄደ (አንድ ስራ)።

**አጣደፈ** ግ 1. አቻኮለ። 2. አዋከበ። 3.ቶሎ ቶሎ አፋጠነ (ስራን፥...)። 4. ፋታ ወይም ጊዜ የማይሰጥ ሆነ።

**አጣዳፊ** ቅ 1. አስቸኳይ፣ በቶሎ መካሄድ፥ መከናወን፥ መሰራት፥ መቅረብ፥... ያለበት። 2. ጊዜ የማይሰጥ (በአጭር ጊዜ ለሞት፥ ለጉዳት፥... የሚያደርስ)። *አጣዳፊ የተቅማጥ በሽታ።*

**ጠዲቅ** "ፀደቀ[1]" ስር "ፀዲቅ"ን ተመ.

**ጠጻ** "ፀጻ"ን ተመ.

**ጠጾ** ስ እንጨትና ቅጠሉ ጌሾ የሚያህልና የሚመስል የእፅዋት አይነት።

**ጠጀ(ጠጀተ)** ግ ጠጅ ጣለ ወይም ጠመቀ።

**ጠጅ** ስ ማርና ጌሾን በማደባለቅ የሚዘጋጅ ቢጫ መልክና አልኮልነት ያለው መጠጥ።

**ጠጅ ጣለ** ጠጅ ጠመቀ ወይም አዘጋጀ።

**ጠጅ ቀጂ** ስ የጠጅ ቤት አሳላፊ፥ አስተናባሪ።

**ጠጅ ቤት** ስ ጠጅ የሚሸጥበትና የሚጠጣበት ቤት።

**ጠጅ አሳላፊ** ስ ጠጅን ለጠጪዎች የሚያድል ወይም የሚያቀርብ።

**ጠጀ ሳር (ጠጅ ሳር)** ስ ነጣ ያለ መልክ ይዞና እንደ እንግጫ ሆኖ የሚበቅል፥ ጥሩ ሽታ ያለው ሻካራ የሳር አይነት።

**ጠገራ[1]** [ብር] ስ ብር ከሚባለው የማእድን አይነት የተሰራና በዱሮ ጊዜ ያገለግል የነበረ ገንዘብ።

**ጠገራ[2]** ስ በአንድ በኩል ብቻ ስለት ያለው፥ ጭንቅላቱ ወፍራም የሆነና ቀጥ ካለ እጀታ ላይ የሚሰካ መጥረቢያ።

**ጠገራ[3]** ስ ለዶማ፥ ለመጥረቢያ፥ ለማረሻ፥... መስሪያ የሚያገለግል ድብልብል ብረት።

**ጠገበ** ግ 1. ሆዱ ሞላ፥ ረካ (በመብል፥ በመጠጥ)። 2. (ዘይ.)ኩራ፥ ማንአለብኝ አለ፥ በትእቢት ተሞላ። 3. ፍቅሩን፥ ናፍቆቱን ተወጣ። 4. በብዛት አገኘ። *መሬቱ ዝናብ ጠገበ።*

**__ጠገብ** ቅ በበቂ ሁኔታ ያገኘ፥ የተገነዘበ፥... ለማለት የሚያገለግል ከፊለ ቃል። *ውሃ ጠገብ / ጆሮ ጠገብ።*

**ጥጉብ** ቅ 1. ያረገዘች (ለአህያ፥ ለፈረስ)። 2. ወፍራም (ለመፅሃፍ)።

**ጥጋብ** ,ስ 1. የሆድ መሙላት፥ እርካታ( በምግብ፥ በመጠጥ)። 2. (ዘይ.) ኩራት፥ ትእቢት፥ ማን አለብኝነት፥ እብሪት። 3. የእህል ችግር የሌለበት ጊዜ።*ዘንድሮ ጥጋብ ነው።*

**ጥጋበኛ** ቅ ትእቢተኛ፥ እብሪተኛ።

**ተጣገበ** ግ ፍቅሩን፥ ናፍቆቱን ተወጣ፥ ጨረሰ (እርስ በርስ)።

**አጠገበ** ግ 1. ሆዱ እስኪሞላ አበላ፥ አጠጣ።2. አረካ (የተበላው ምግብ፥ መጠጥ)። 3. ትእቢተኛ፥ እብሪተኛ፥ ኩራተኛ እንዲሆን አደረገ። 4. በብዛት በመስጠት፥ በማስገኘት፥ በማቅረብ፥... አረካ። *ዝናቡ አጠገበ።*

**አጥጋቢ** ቅ የሚያረካ፥ ደስ የሚያሰኝ፥ ብቃት ያለው፥ ...።

**ጠገነ** ግ 1. የተሰበረን አጥንት አስሮ እንዲድን አደረገ። ቅ 2. የተጎዳ፥ የተበላሸን ነገር አስተካከለ፥ አበጀ፥ አደሰ፥ ደህና አደረገ።3. (ዘይ.) ጠቀመ፥ ደገፈ፥ ረዳ።

**ጠጋኝ** ስ 1. የእድሳት ስራ የሚሰራ የእጅ ባለሙያ። ቅ 2. መሰረታዊ ለውጥ ሳይሆን የነበረውን ሁኔታ በመጠኑ በማሻሻል ብቻ ለውጥ ለማድረግ የሚሞክር የፖለቲካ አዝማሚያ ያለው።

**ጥገና** ስ የተሰበረ፥ የተጎዳ፥ የተበላሸ እቃን ማስተካከል፥ ማደስ፥ ማበጀት።

**ጥገናዊ ለውጥ** ስ መሰረታዊ ያልሆነና በነበረው ላይ ብቻ መጠነኛ የሆነ መሻሻልን የሚያስከትል ለውጥ።

**ጥግን** ቅ ተሰብሮ፥ ተበላሽቶ የነበረና የተሰራ ወይም የታደሰ (እቃ)።

**አስጠገነ** ግ አሰራ፥ አስበጀ(የተበላሸን፥ የተሰበረን እቃ)።

**ጠገነነ** ግ ዘገነነ፥ ሰቀጠጠ፥ አሰቆጣ።

**ጠገገ** ግ መጠጥ አለ፥ ደረቀ (ቁስል፥ ጭቃ)።

**ጠገግ[1]** ስ ፍራሽ ወይም ጉዝጓዝ የሌለው የእንጨት አልጋ፥ ቆጥ፡፡

**ጠገግ[2]** ስ የሰንሰለት አንዱ ሞላላ ቀለበት።

**ጠጉር** "ፀጉር"ን ተመ.

***ጠጋ**

**ጥግ (ጥጋት)** ስ ተገን ያለው ወይም በኮረብታ፥ በግድግዳ፥... አጠገብ ወይም ስር የሚገኝ ቦታ።

**ባለጥግ** ባለወገን።*ጠላቴ ባለጥግ ስለሆነ ልረታው አልቻልኩም።*

**ጥግ ያዘ** 1. ተጠጋ፥ ጥግ ላይ ሆነ። 2.ደህና ቦታ ወይም ስፍራ፥... ያዘ።

**ጥጋጥግ** ስ የተራራ፥ የኮረብታ፥ የገደል ስር።

**ጥገኛ** ቅ 1. ራሱን ያልቻለ፥ በሌላ እርዳታ የሚኖር። 2. በሌላው አካል ወይም ድርጅት ጥላ ስር የሚንቀሳቀስ (ንኡስ ክፍል)። 3. ኑሮው፥ ህልውናው፥ ህይወቱ በሌላው ላይ የቆየ (የነፍሳት ወይም የእፅዋት አይነት)።

**ጥገኛ ሃረግ** ስ የማያስር አንቀፅ ያለበት የአረፍተ ነገር ንኡስ ክፍል።(ለምሳሌ "ከሄድኩ አልመጣም"። በሚለው አ.ነገር ውስጥ "ከሄድኩ" የሚለው ጥገኛ ሃረግ ነው)።

**ጠጋ አለ** ግ ቀረብ አለ (በአካል፥በስሜት፥ በአስተያየት፥ በመጠን፥...)።

**ጠጋ አደረገ** ግ አቀረበ፥ አስጠጋ።

**ተጠጋ** ግ 1. ቀረበ፥ ጠጋ አለ። 2. ጥገኛ ሆነ፥ በሌላ ሰው እርዳታ ኖረ። *ከሃብታም ተጠግቶ ይኖራል።* 3.አከለ፥ ደረሰ።*የተሸለሙት ሰዎች ወደ ሺህ ተጠግተዋል።* 4. ተከለለ፥ ተገን አደረገ።*ጅብን ሲወጉ በአህያ ይጠጉ።*

**አይጠጋውም** ምንም ያህል ቢበላ ሰውነት አይሆነውም፤ አይጠረቃም።

**መጠጊያ** ስ 1. ከአደጋ መሸሸያ፥ ከፉ ጊዜን ማሳለፊያ (ሰው፥ ቦታ፥...)። 2. መጠለያ።

**ተጠጋጋ** ግ 1. ተቀራረበ። 2. ከአንድ በታች የሆነ ክፍልፋይ ቁጥር ከግማሽ በላይ በመሆኑ ወደሙሉ ቁጥርነት ተለወጠ (ለምሳሌ፥ 5.6 ሲጠጋጋ 6.00 ይሆናል)።

**ተጣጋ** ግ ከሳ፥ ቀነነ።

**አጠጋጋ** ግ 1. አቀራረበ። 2. ከግማሽ በላይ የሆነ ክፍልፋይ ቁጥርን ወደ ሙሉ ቁጥር ለወጠ።

**አጣጋ** ግ 1. አጋጨ፥ አላተመ፥ መታ። 2. ክፍልፋይ ቁጥርን ወደ ሚቀርበው መጠን አሸጋሸገ፥ ለወጠ። (ለምሳሌ፥ 2.7 ሲጣጋ 3. ይሆናል)።

**አስጠጋ** ግ 1. አቀረበ፥ አንዱን ነገር ከሌላ ጎን ወይም አጠገብ አስቀመጠ። 2. መጠጊያ ሆነ፥ ረዳ።

**ጠጋኝ** "**ጠገነ**" ስር ተመ.

**ጠጠረ** ግ 1. ጠነከረ፥ በረታ፥ ጠና። 2. ደደረ፥ እንደ ጠጠር ሆነ።3. (ዘይ.) ከበደ፥ ቀላል አልሆን አለ።

**ጠጠር** ስ 1. ትናንሽ ወይም ጥቃቅን ድንጋይ። 2.እንደ ልቅምሽ፥ ገበጣ፥ ዳማ፥... ያሉ ጨዋታዎችን ለመጫወት የሚያገለግሉ መጫዎቻዎች።

**ጠጠር ጣይ** ስ ጠጠር እየበተነ ወይም እየጣለ ይህ ይሆናል ወይም ይህ ይደረጋል የሚል ጠንቋይ ።

**ጠጣር** ቅ 1. ጠንካራ። 2. ፈሳሽ ያልሆነ 3.(ዘይ.) ከባድ፥ አስቸጋሪ።

**ጥጥር** ዝ.ከ.

**ጠጣ** ግ 1. ወደ ሆዱ አስገባ፥ ዋጠ፥ ፉት አለ፥ ጨለጠ (ፈሳሽን)። 2. ወሰደ፥ ተጎነጨ (አልኮል መጠጥን)። 3. አጨሰ፥ ማገ፥ መጠጠ። (ሲጋራን፥ ትንባሆን)። 4.መጠጠ። *ወረቀቱ ቀለሙን ጠጣው።* 5. ውሃ ተጨመረበት፥ ፈሰሰበት (አትክልት፥ ግንብ፥...)።

**መጠጥ** ስ 1. በፈሳሽ መልክ ተዘጋጅቶ የሚጠጣ ነገር። 2.አልኮልነት ያለውና የሚጠጣ ፈሳሽ። *መጠጥ ሲበዛ ለጤና ጠንቅ ነው።*

**መጠጥ አወረደ** መጠጥ በሳጥን ወይም በጅምላ ገዛ (ለመጠጥ ንግድ ቤት)።

**መጠጫ** ስ 1. እንደ ኩባያ፥ ዋንጫ ያለና ለመጠጫነት የሚያገለግል እቃ። 2. እንደ ሸንበቆ ያለ የጋያ መሳቢያ (የትንባሆ ጭስ መማጊያ)።3. ለመጠጥ የሚሆን ገንዘብ። *መጠጫ ሲያጣ በጊዜ ይገባል።*

**የመጠጥ ውሃ** ስ ለመጠጥ የሚሆን ውሃ።

**ጠጪ** ቅ 1. ሰካራም፤ መጠጥ የሚያበዛ። ስ 2. ወደ መሸታ ቤት በመሄድ መጠጥ እየገዛ እዚያው ቁጭ ብሎ የሚጠጣ ደንበኛ።

**ተጣጣ** ግ 1. ተቻቻለ፥ እዚያው በዚያው ሂሳቡ ተወራረደ፥ ተከፈለ። 2. እየተጠራራ፥ እየተገባበዘ ጠጣ (ቡናን፥ ጠበል ጠዲቅን)።

**አጠጣ** ግ 1. ውሃን ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገርን እንዲጎነጭ ሰጠ። 2. ውሃ ጨመረ፥ አፈሰሰ (አትክልት፥ ግንብ፥... ላይ)። 3. መጠጥ ጋበዘ። 4. በገበጣ ጨዋታ ጊዜ በውጣ ላይ ጠጠር ጨመረ፤ ወይም በካርታ ጫወታ ጊዜ በበላው ካርታ በተጨማሪ ተመሳሳይ ቁጥር ያለውን ካርታ ጨመረ።

**አስጠጣ** ግ (ያራዳ አነ.) እንዲታወቅ አደረገ፥ አጋለጠ።

**ጠፈረ**[1] ግ 1. አጥብቆ አሰረ፥ ቀፈደደ። 2. ማገረ፥ አዋቀረ፥ ታታ (የቤትን ጣራ፥ ግድግዳ)።

**ጠፍር** ስ ከከብት ቆዳ ተተልትሎ የተዘጋጀ ማሰሪያ።

**ጠፍር ነካሽ** "**ጫኑ**" ስር "**መጫኛ ነካሽ**"ን ተመ.

**ጠፈረ**[2] ግ በጥፊ መታ፥ አጮለ።

**አጣፈረ (አጠናፈረ)** ግ በጥፊ መታ፥ አጮለ።

**ጠፈር** ስ ከምድር ከባቢ አየር ውጪ ያለ ቦታ፤ ሰማይ።

**ጠፈርተኛ** ስ ለልዩልዩ ስራ ወይም ምርምር በመንኮራኩር ወደጠፈር የሚሄድ ወይም የሚላክ ሰው።

**የጠፈር መንኮራኩር** ስ በጠፈር ውስጥ መጓዝ የሚችል ሰው ሰራሽ በራሪ አካል።

**ጠፈጠፈ** ግ 1. ወፍራም ሊጥን በምጣድ ላይ ዘረጋጋ (ለመጋገር)። 2. የከብት እበት ኩበት እንዲሆን በመሬት ላይ በእጁ እየተመተመ ዘረጋጋ። 3. (ዘይ.) ደጋግሞ በጥፊ መታ።4. ጠፍጣፋ ወይም ዝርግ አደረገ (ደጋግሞ በመቀመጥ፥ በመምታት፥...)።

**ጠፍጣፋ** ቅ ድብልብል ወይም ሞላላ ያልሆነ፥ ዝርግ።

**ጥፍጥፍ** ስ 1. የተጠፈጠፈ የከብት እበት። ቅ 2. (ዘይ.) ድፍጥጥ፥ አፍንጫው ቀጥ ያላለ።

***ጠፈጠፈ**

**ጠፈጠፍ** ስ ዝናብ ከዘነበ በሏላ ከቤት ጣሪያ፥ ከዛፍ ቅርንጫፍ፥ ከጃንጥላ ላይ የሚንጠባጠብ የዝናብ ውሃ፤ ፍሳሽ።

**ተንጠፈጠፈ** ግ እየተንጠባጠበ ፈሶ አለቀ፥ ደረቀ (ውሃ አዝሎ የነበረ ነገር)።

**አንጠፈጠፈ** ግ እያንጠባጠበ አፈሰሰ፥ አደረቀ (ፈሳሽን)።

**እንጥፍጣፊ** ቅ 1. እቃ ላይ የቀረ ትንሽ ፈሳሽ፥ ጭላጭ። 2. ሙጣጭ።

**ጠፈፈ** ግ መጠጠ፥ መድረቅ ጀመረ።

**ጠፍታ** ስ ዝርክርክነት የሌለበት ሁኔታ።

**ጠፈፍ አለ** ግ መጠጥ፥ ደረቅ አለ።

**ጠፍ አለ** ግ 1. መጠጠ፥ ደረቀ። 2. (ዘይ.) ንፁህ፥ ዝርክርክነት የሌለው ሆነ። *ጠፍ ያለች የቤት ወይዘሮ።*

**ጠፉ**[1] ግ 1. ታጣ፥ አልገኝ አለ፤ ወደ አለመኖር ተለወጠ። 2.ሳያሳውቅ ሄደ፥ ኮበለለ፥ አድራሻውን ሰወረ። 3. እልም አለ፥ ተደረገመ(አይን፥ እሳት፥...)። 4. ሞቶ ተወለደ ወይም እንደተወለደ ሞተ (ህፃን)። 5. ተበላሸ፥ መጥፎ ሆነ (ልብስ ወይም ሌላ እቃ)። 6. ተረሳ፥ ተዘነጋ።*ስሙ ጠፋብኝ።* 7. ምግባሩ፥ ጠባዩ ተበላሸ፥ ተለወጠ። 8. ወጪ ሆነ። *ለማስተንገዶ ብዙ ገንዘብ ጠፋ።* 9. ለቀቀ፥ ተወ። *ፍርሃቱ ጠፋለት።* 10. ሳይመጣ ወይም ሳይታይ ቆየ። *ሰሞኑን ጠፋህ፤ አላገኘሁህም።* 11.ተሰረዘ፥ የማይታይ ወይም የማይነበብ ሆነ (ፅሁፍ፥...)።

**የጠፋ** የማይታወቅ። *ውሉ የጠፋ /መፍትሄው የጠፋ።*

**መጥፎ** ቅ 1. አስቀያሚ፥ የማያምር። 2. ክፉ፥ ተንኮለኛ፥ ጠባየ ብልሹ። 3. የማይስማማ፥ የማይመች፥ ጥሩ ያልሆነ(ጊዜ፥ ቦታ፥...)።

**ጠፊ** ቅ 1. ጟች። *ሁሉም ሳላፊ ጠፊ ነው።* 2. አላፊ።*ሃብት ጠፊ ነው።*

**ጠፍ** ቅ 1. ያልታረሰ፥ ያልለማ (መሬት)። 2. ለምነት የሌለው (መሬት)።3. ባለቤት የሌለው (ብዙውን ጊዜ ለከብት)።*የጠፍ ከብት።*

**ጠፍ ሆነ** ባድማ ሆነ።

**ጠፍ ከለም** ቅ ከፊል ለም ከፊል ጠፍ የሆነ (መሬት)።

**ጠፍ ጨረቃ** ስ የጨረቃ ብርሃን የማይታይበት፥ ድፍን ጨለማ የሆነበት ሌሊት።

**ጥፉ** ቅ 1. ብልሹ፥ ጠባየ መጥፎ። 2. የማያምር፥ አስቀያሚ፥ ደስ የማይል (መልክ)።

**ጥፋት** ስ 1. ስህተት፥ ትክክል ያልሆነ ስራ። 2. ከህግ፥ ከደንብ ውጭ የተፈፀመ ድርጊት።*ተጫዋቹ ጥፋት ስለሰራ የቅጣት ምት ተሰጠ።* 3. ጉዳት፥ ብልሽት።*ጎርፉ በንብረት ላይ ጥፋት አደረሰ።*

**ጥፋተኛ** ቅ 1. ወንጀለኛ። 2. ስህተተኛ፥ በደል የፈፀመ።

**ጥፌ** ቅ ባለቤቱ ያልታወቀ ወይም ወድቆ የተገኘ (ለምሳሌ ገንዘብ)።

**ተጣፋ** ግ (ሂሳ.) ክፍልፋይ ቁጥር ያለቀሪ ሊያካፍል በሚችል ቁጥር ተከፋፈለ። ለምሳሌ 2/4 በሁለት ሲጣፋ ½ ይሆናል።

**ተጠፋፋ** ግ ሳይገናኝ ቀረ፥ ተጣጣ፥ አንዱ የሌላውን አድራሻ አጣ።

**አጠፋ** ግ 1. ረሳ፥ ዘነጋ (ያውቀው የነበረውን)። 2. አባከነ (ገንዘብን፥ ጊዜን፥...)። 3. ተሳሳተ፥ ትክክል ያልሆነ ድርጊት ፈፀመ። 4.ገደለ፤ ጨረሰ፥ አወደመ። *መድሃኒቱ ተባዮችን አጠፋቸው።* 5. አበላሸ፥ አጎደፈ፥ ጉዳት አደረሰ።6. መጥፎ ጠባይን አስተማረ። 7. ከህግ፥ ከደንብ ውጭ የሆነ ነገር ፈፀመ። 8. አስወገደ፥ እንዳይኖር አደረገ። *ስራ አጥነትን አጠፋ።* 9. እንዳይታይ፥ እንዳይታወቅ፥ እንዳይሰማ አደረገ።*አድራሻውን፥ አጠፋ።* 10. አንድ ነገር እንቅስቃሴውን፥ ስራውን እንዲያቆም አደረገ።*ሞተሩን አጠፋ /መብራቱን አጠፋ።*

**አጥፊ** ቅ 1.ወንጀለኛ። 2. ስህተተኛ፥ በደል ፈፃሚ። 3. ጠባየ ብልሹ፥ ስርአት የለሽ።

**አጥፊና ጠፊ** ገዳይና ጟች።

**አጠፋፋ** ግ 1. ደባበቀ፥ ሸፋፈነ (መረጃን)። 2. ጨረሰ፥ አባከነ (ገንዘብን)።

**አጣፋ** ግ ክፍልፋይ ቁጥሮችን ያለቀሪ ሊያካፍለው በሚችል ቁጥር አቃለለ፥ አካፈለ። (ለምሳሌ፥ 2/4 በሁለት ሲያጣፉት 1/2 ይሆናል)።

**ጠፉ**[2] ግ 1. በጥፊ መታ፥ አጮለ። 2. እንዝርትን ለማሽከርከር በጭን ላይ አፍተልትሎ አሾረ።

**ጥፊ** ስ 1. ውስጥ እጅ (ከመዳፍ እስከ ጣት ጫፍ ያለው የእጅ አካል)።2. በውስጥ እጅ አማካይነት የሚደረግ ምት። 3. ከአይን ስር ያለው ቆዳ እብጠት በሽታ።

**በጥፊ ከደነበት/ላሰው/ አላሰው/ መረገበት** በጥፊ መታው።

**ተጣፋ** ግ ምች ወይም ሽውታ የታችኛውን የአይን ሽፋን አሳበጠ።

**አጣፋ** ግ 1. ጋቢን ወይም ኩታን ዘርግቶ በቀኝና በግራ ትከሻው ላይ ጣል በማድረግ ለበሰ። 2. በጥፊ መታ፥ አጮለ።

**ጠፍ** "**ጠፉ**[1]" ስር ተመ.

**ጠፍር** "**ጠፈረ**[1] " ስር ተመ.

**ጠፍታ** "**ጠፈፈ**" ስር ተመ.

**ጠፍጣፋ** "**ጠፈጠፈ**" ስር ተመ.

**ጡ** የ "**ጠ**" ፊደል ካእብ ዘር።

**ጡሊ**[1] ስ መንገደኛ ውሃ የሚይዝበት ቅል፤ ቅምጫና።

**ጡሊ**[2] "**ጡል**" ስር ተመ.

**ጡል**

**ጡሊ** ቅ ቀዥቃዣ፥ ዘዋሪ፥ ከውካዋ።

**ጡል ጡል አለ** ግ ወዲያ ወዲህ ተመላለሰ፥ ተንከወከወ፥ ተንቀዠቀዠ።

**ጡረተኛ** "ጡረ" ስር ተመ.

**ጡረታ** ዝ.ከ.

**ጡር** ስ ግፍ፥ በደል።

**ጡር ሰራ** በደለ፥ ግፍ ፈፀመ።

**ጡር አለበት** ግፍ ሰርቷል፥ በድሏል።

**ጡረኛ** ቅ ግፈኛ፥ በደለኛ።

**ጡብ** ስ ከሸክላ አፈር የሚሰራና አራት ማእዘንነት ያለው፥ ለግንብ መስሪያ የሚሆን ሸክላ።

**ጡብ**

**ጡብ አለ** ግ 1. ከላይ ወደ መሬት ዘሎ ወረደ፣ ዱብ አለ። 2. ዘለለ፥ እንጣጥ አለ።

**ጡብ ጡብ አለ** ግ ዱብ ዱብ፥ እንጣጥ እንጣጥ አለ፥ ዘለለ።

**ጡት** ስ 1. በሰው ደረት ወይም በእንስሳት ጉያ ላይ ተንጠልጥሎ የሚገኝ፥ ልጆቻቸው የሚመገቡትን ወተት የሚያመነጭ የሰውነት ክፍል (በወንዶች ላይ ያለው ግን ትንንሽ ከመሆኑም ሌላ ወተት አይወጣውም) (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)። 2. በማንቆርቆሪያ፥ በኩስኩስት፥... ጎን በኩል ወጣ ብሎ የሚገኝ የፈሳሽ ማውረጃ ቀዳዳ።

**ጡት ተጣባ** የጡት ልጅና የጡት አባት ወይም እናት በመሆን ተዛመደ።

**ጡት አጠባ** የጡት ልጅ አደረገ።

**ጡት ጠባ** የአንድን ሰው በማር የተቀባ አውራ ጣት በጡት ምሳሌ በመጥባት ተዛመደ፥ ልጁ ሆነ።

**ጡት ጣለ** ጡት መጥባት ተወ።

**የጡት ልጅ** ስ ከትውልድ ሃረግ ውጭ የሆነና የአንድን ሰው በማር የተነከረ አውራ ጣት በመጥባት እንደ ልጅ ሆኖ የተዛመደ ሰው።

**የጡት መያዣ** ስ ሴቶች ጡታቸውን ደግፎ እንዳይዝላቸው የሚያደርጉበት፥ ብዙውን ጊዜ ማንገቻ ያለው አነስተኛ የጡት መደገፊያ ልብስ ።

**የጡት አባት** ስ የጡት ልጅ ለሚሆነው ሰው (ከትውልድ ሃረግ ውጭ ለሆነ) በማር የተነከረ ጣቱን በማጥባትና ቃል ኪዳን በመግባት እንደ አባት ሆኖ የተዛመደ ሰው።

**የጡት እናት** ስ የጡት ልጅ ለሚሆነው ሰው (ከትውልድ ሃረግ ውጭ ለሆነ)በማር የተነከረ ጣቷን በማጥባትና ቃል ኪዳን በመግባት እንደ እናት ሆና የተዛመደች ሴት።

**ጡት አስጣይ** ስ ተከታይ ታናሽ ወንድም ወይም እህት።

**ጡንቻ** ስ 1. የመለጠጥና የመጠጠር ባህርይ ያለው፥ ከትከሻ እስከ ክርን ባለው የክንድ ክፍል ላይ የሚገኝ ፍርጥም ያለ ስጋ። 2. በሰውና በእንስሳት ሰውነት ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚገኝ፥ የመለጠጥና የመኮማተር እንዲሁም የመሰብሰብ ባህርይ ያለውና ለእንቅስቃሴ የሚያስፈልግ ጠንካራ ስጋ። 3. (ዘይ.) ሃይል፥አቅም፥ ጉልበት።*ጡንቻውን ላሳዮ።*

**ጡንቻውን አዳበረ** (ስፖ.) የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በመስራት ጡንቻውን አዳበረ፥ አፈረጠመ።

**ጡንቸኛ** ቅ ሃይለኛ፥ ጉልበተኛ፥ ተደባዳቢ (ሰው)።

**ጡን ጡን አለ** "ጠነጠነ" ስር ተመ.

**ጡዘት** "ጠዘ" ስር ተመ.

**ጡዝ**

**ጡዝ አደረገ** ግ ፈሳ፥ አንዛረጠ።

**ጡጥ**

**ጡጥ አለ** ግ አነስና አጠር ያለ የፈስ ድምፅ ተሰማ ቀቅ አለ።

**ጡጥ አደረገ** ግ አነስና አጠር ያለ ድምፅ ያለው ፈስ ፈሳ።

**ጡጥም ከፈስ ተቆጠረች** በጣም ትንሿም ጉዳይ እንደ ትልቅ ቁም ነገር ታየች ወይም ተቆጠረች ለማለት የሚነገር።

**ጡጦ** ስ ህፃናት ወተት ወይም ሌላ ፈሳሽ የሚመገቡበት (እንደ ጡት የሚመጠምጡት ወይም የሚጠቡት) ከፕላስቲክ የሚሰራ ጠርሙስ መሰል እቃ ና በአፍ የሚጠጣው ጫፍ በአንድነት ወይም በተናጠል የሚጠሩበት ስም (የሚጠባው ጫፍ የጡጦ ጫፍም ይባላል)።

**ጡጦ አይጠባም** ህፃን አይደለም፥ አይታለልም።

**ጡጫ** ስ የታጠፈ ወይም የተጨበጠ የእጅ ጣት፥ ቡጢ።

**ጡጫ ሆድ** ስ የተወጠረ ወይም የተቆዘረ ሆድ።

**ጢ** የ "ጠ" ፊደል ሳልስ ዘር።

**ጢል**

**ጢሎሽ** ስ የዛፍን ቅርንጫፍ በማዝመም ወይም ገመድን እንጨት ላይ በማሰርና በላዩ ላይ በመንጠልጠል እየተወዛወዙ የሚጫወቱት እንደ ጅዋጅዌ ያለ የልጆች ጨዋታ።

**ጢል አለ** ግ ተንጠለጠለ፥ ተሰቀለ።

**ጢም** "ፂም"ን ተመ.

**ጢም አለ** ግ በጣም ሞላ።

**ጢር አለ** ግ ከራ፥ ታበየ፥ ተጀነነ።
**ጢራ** ቅ ኩሩ፥ ጅንን።
**ጢሰኛ** "ጪሰ" ስር "ጪሰኛ"ን ተመ.
**ጢስ** "ጪስ" ስር "ጪስ"ን ተመ.
**ጢሻ** "ጥሻ"ን ተመ.
**ጢቅ**[1]
**ጢቅ አለ** ግ ሞላ፥ ጢም አለ።
**ጢቅ አደረገ** ግ ሞላ፥ በብዛት ከተተ፥ ጠቀጠቀ (ሻንጣን፥..)።
**ጢቅ**[2]
**ጢቅታ** ስ አፈናጥረው የተፉት ምራቅ።
**ጢቅ አለ** ግ 1. ምራቁን በጥርሶቹ መካከል አፈናጥሮ ተፋ። 2. (ዘይ.) ተፀየፈ፥ አጥላላ።
**ጢብኛ** "ጥብኛ" ን ተመ.
**ጢን**
**ጢን አለ** ግ 1. ሞላ፥ ጢም አለ። 2. (ዘይ.) ኩራ፥ ተንቀባረረ። 3. (ዘይ.) በጣም ሰከረ።
**ጢንጦ** ስ ከሌሎች ጋር በመካፈል የሚገኝ አነስተኛ መሬት።
**ጢው**
**ጢው አለ** ግ ጮሀ፥ ጡጥ አለ (ፈስ)።
**ጣ**[1] የ "ጠ" ፊደል ራብእ ዘር።
**ጣ**[2]
**ጣ አለ** ግ እሳት ሲነድ ወይም ሲፈናጠር የሚያሰማውን አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ።
**ጣለ** ግ 1. ወረወረ፥ አሽቀነጠረ። 2. ደበለለ፥ ዘረረ (በትግል) ። 3. እንዲወድቅ፥ እንዲጠፋ አደረገ። *ብር ጣለ።* 4. ገነደሰ፥ ከሰሩ ቆረጠ (ዛፍን)። 5. መገልገል፥ መጠቀም ተወ (አንድን እቃ)። 6. አእምሮውን ስቶ እንዲወድቅ አደረገ (ብዙውን ጊዜ የአእምሮ ህመም)። 7. ከፈለ (የእቁብ መዋጮውን)።8. መታ፥ ገደለ ወይም አቆሰለ (በመሳሪያ)። 9. በርካሽ ሸጠ። 10. እንዳያልፍ አደረገ (በፈተና)። 11. ተወ። *ሰውዬውን ጥሎ ሄደ።* 12. ወሰነ፥ መደበ። *መቀጫ ጣለ።* 13. (የን.አነ.) ሰጠ።*በየወሩ ትንሽ ገንዘብ ይጥልለታል።*
**በ ___ ላይ ጣለ** በ __ ላይ አሳረፈ። *ሃላፊነቱን በእሱ ላይ ጣለ።*
**ጣለበት** 1. አይኑን ጋረደው፥ ከለለው፥እንደልብ ማየት ተሳነው፥(በበሽታ ምክንያት)። 2. አዘዘበት፥ ፈረደበት።
**ጣል አደረገ** ግ ተወት አደረገ፥ ችላ አለ።
**ጣል ጣል አደረገ** ግ አራከሰ፥ አዋደቀ፥ አጣጣለ።
**ጥሎ ማለፍ** ስ (ስፖ.) በተለያዩ ብዙ ቡድኖች መካከል በሚደረግ የእግር ኳስ ወይም ሌላ ውድድር ላይ ተሸናፊው ቡድን እየወጣና አሸናፊው ቡድን ወደሚቀጥለው ደረጃ እያለፈ ቀሪዎቹ የሚጋጠሙበት የውድድር ሂደት።
**መጣያ** ስ ሚዛኑን ለማስተካከል በጭነት ላይ የሚጨመር ትንሽ ነገር።
**ጣጣለ** ግ ተው።
**ጣጥሎ ሄደ** ግ ትቶ ሄደ (እቃውን፥ ንብረቱን፥ቤቱን፥...)።
**ጥለት** ስ 1. በፊት ላይ የሚወጣና ፊትን የሚያጠቁር ማዲያት። 2. (ዘይ.) የእግዚአብሄር ቁጣ፥ መአት።
**ጥሎሽ** ስ በጋብቻ ስነስርአት ላይ ከሙሽራው ለሙሽራዋ የሚሰጥ ገፀበረከት፥ ስጦታ።
**ተጣለ** ግ ተተወ፥ ከጥቅም ውጭ ሆኖ ወደቀ።
**አጣጣለ** ግ አዋደቀ፥ አራከሰ።
**አጣጣል** ስ አፃፃፍ (የፊደል)።
**አስጣለ** ግ 1. አዳነ፥ አተረፈ (ከአደጋ፥ ከጉዳት፥..)። 2.አስተወ።
**ጣልቃ** "ጠለቀ[1]" ስር ተመ.
**ጣመ** ግ 1. ጣፈጠ፥ ጥሩ ጣእም ኖረው (ምግብ፥ መጠጥ፥...)። 2. ደስ አሰኘ፥ አረካ (ንግግር፥ ፅሁፍ፥ ስራ ፥...)። *ንግግሩ ጣመኝ።*
**ጣእም** ስ 1. የአንድ ነገር የጣፋጭነቱ ወይም የመራራነቱ ስሜት።*ጣእሙን አልቀመስኩትም።* 2. ጣፋጭነት።*ጣእም አለው።* 3.ዋጋ፥ ጠቀሜታ፥ ጥሩነት። *የእናት አባት ጣእም/ የገንዘብ ጣእም።* 4. አስደሳችነት፥ ውበት።
**ጣእም አጣ** 1. አልጣፍጥ አለ። 2. ለዛ አጣ፥ አስጠላ፥ ቸከ።
**ጣእመ ቢስ** ቅ ለዛ የሌለው፥ የማያስደስት።
**ጣእመ ዜማ** ስ የሚስብ ወይም የሚያስደስት የዜማ ቃና ።
**ተጣጣመ** ግ ተስማማ፥ ተዋደደ፥ አብሮ የሚሄድ ሆነ።
**የማይጣጣም** የማይስማማ፥ አብሮ የማይሄድ።
**አጣጣመ** ግ 1. ጣእምን ለመለየት በምላሱ ፈተሸ፥ ቀመሰ ። 2. አብላላ፥ ተገነዘበ (ነገርን)። 3. አስማማ፥ አብሮ እንዲሄድ አደረገ። 4. አደነቀ። *ስነፅሁፍን የማጣጣም ችሎታ አለው።*
**ጣመነ** ግ ደከመ፥ ዝሎ (ሰውነት)።
**ጣመን** ስ ከጉዞ ወይም ከጉልበት ስራ የሚመጣ ድካም፥ የሰውነት መዛል።
**ጣማ**
**ጣማ ገንዘብ** በገዛ ራስ ድካም፥ በልፋት የተገኘ የሃቅ ገንዘብ።
**ጣምራ** "*ጠመረ" ስር ተመ.

**ጣረ** ግ ተጣጣረ::

**ጥረት** ስ ልፋት+ ትጋት+ ድካም (አንድ ነገር ለማግኘት+ ለመስራት+...)::

**ተጣጣረ** ግ ለፋ+ ደከመ+ ታገለ+ ብርቱ ሙከራ አደረገ (ከአላማ ለመድረስ)::

***ጣረ**

**ጣር(ፃእር)** ስ 1.'ጭንቀት+ ስቃይ::2.ነፍስና ስጋ በሚለያዩበት ጊዜ የሚሰማ ፅኑ የሆነ የህመም ስሜትና ስቃይ::

**ጣር በዛበት** በጣም ተሰቃየ፤ ነፍሱ ከስጋው በቶሎ አልለይ አለች::

**ጣረ ሞት (ፃእረ ሞት)** ስ አለልክ ቀጭንና እስጠሊታ+ ሞጋጋ የሆነ ገፅታ::

**ጣረ ሞት (ፃእረ ሞት) ይዞታል** እያጣጣረ ነው::

**አጣጣረ** ግ ጣር ላይ ሆነ፤ ሊሞት ደረሰ::

**ጣራ (ጣሪያ)** ስ 1. ከግድግዳ በላይ ያለ የቤት መዋቅር+ ባጥ+ ክዳን::2. የከፍታ መጠን:: *የደመወዙ ጣሪያ አምስት መቶ ብር ነው::*

**ጣር** "*ጣረ" ስር ተመ.

**ጣሰ** ግ 1. ሰበረ+ አፈረሰ:: 2. በሃይል አለፈ+ ገፍቶ አልፎ ሄደ:: 3. ተላለፈ+ አፈረሰ (ህግን+ ስርአትን...):: 4. ጎፈሬ የነበረውን ፀጉር ሹርባ ሰራ:: 5. ፈጠ (አሸርን)::

**ተጣሰ** ግ ፈረሰ+ ሳይከበር ቀረ (ህግ)::

**ጣሰሰ** ግ ለሸለሸ+ አጋደመ (ሜካን)::

**ጣሳ** ስ ከቆርቆሮ የሚሰራና ለመያዣ+ ለመጥለቂያ+ ለመስፈሪያ የሚያገለግል የቤት እቃ ወይም ቁሳቁስ::

**ጣቃ** ስ ያልተሰፋ+ ትልቅና ጥቅል የሆነ ብትን ጨርቅ::

**ጣቢያ** ስ 1. የአንድ ተግባር ማከሄጃ ቦታ ወይም መስሪያ ቤት:: *የምርምር ጣቢያ /የእርሻ ጣቢያ::* 2. ፖሊስ ስር "**ፖሊስ ጣቢያ**"ን ተመ.

**ጣባ** ስ ትርፁ ጎድጓዳ ሳህን የመሰለና ከሸክላ ወይም ከእንጨት የሚሰራ የቤት እቃ (ስእሉን የ"**ሸክላ እቃ**" ስር ተመ.)::

**ጣብቂያ** "*ጠበቀ[1]" ስር ተመ.

**ጣት** ስ በእጅና በእግር ጫፍ ላይ የሚገኝና አንጓ ያለው ተንቀሳቃሽ የሰውነት ክፍል::

**ጣቱን ቀሰረበት** ዛተበት+ በተቃዋሚነት ወይም በጠላትነት ተነሳበት::

**ጣቱን ይጠባል እንዴ!** እንደ ህፃን ይታለላል ወይ!

**የጣት ቤዛ** ስ ልብስ የሚሰፋ ወይም የሚዘመዝም ሰው መርፌው ጣቱን እንዳይወጋው በሌባ ጣቱ ላይ የሚሰካው መከላከያ ፤ ከስቱባን::



የጣት ቤዛ

**የጣት ወርቅ** ስ ከወርቅ የተሰራና በእጅ ጣት ላይ የሚደረግ ጌጥ::

**የጣት ውሃ** ስ ለእጅ መታጠቢያ የሚቀርብ ውሃ::

**የጣት ፊርማ** ስ ጣትን ቀለም በማስነካትና አሻራን ብወረቀት ላይ በማሳረፍ የሚፈረም ፊርማ::

**ጣእም** "ጣመ" ስር ተመ.

**ጣኦት** ስ ሰዎች እንደ አምላክ የሚያመልኩበት ድንጋይ+ ዛፍ ወይም ከድንጋይ+ ከእንጨት+... የሚሰራ ምስል::

**ጣውላ** ስ 1. ተሰንጥቆ የተላገ እንጨት:: 2. ከተላገ እንጨት የተሰራ የቤት ወለል::

**ጣውንት** ስ ጎባን፤(አንዲት ሴትን በተለያየ ጊዜ ያገቡ ወንዶች ወይም አንድን ወንድ በተለያየ ጊዜ ያገቡ ሴቶች እርስ በርሳቸው ያላቸው ግንኙነት መጠሪያ::

**ጣምስ** ስ ጅራቱ የሚብለጠለጭ+ አንገቱና ራሱ ሰማያዊ መልክ ያለው ተለቅ ያለ ወፍ፤ ኢፌ ገነትም ይባላል:: (ስእሉን "**ወፍ**" ስር ተመ.)

**ጣዝማ** ስ ከንብ አነስ ከትንኝ ከፍ የምትልና ማሯን በመሬት ውስጥ የምትጋግር የነፍሳት አይነት::

**ጣዝሙት** (ዘይ.) ልባም+ ባለሙያ (ሴት)::

**ጣዝማ ማር** ስ ጣዝማ የምትሰራው ወለላ ማር::

**ጣደ** ግ ለማብሰል+ ለመቀቀል ወይም ለማፍላት እሳት ላይ ወይም እሳት ያለበት ምድጃ ላይ አስቀመጠ (ምጣድን+ ድስትን+...)::

**ጥዶ ዘለል** ቅ 1. ከውካዋ+ ወፈፌ:: 2. የጣደችውን ሳታወጣ ወይም ስራው ሳያልቅ ትታው ወሬ ፍለጋ የምትዞር::

**ምጣድ** ስ ከሸክላ ወይም ከብረት የሚሰራ ለእንጀራ+ ለዳቦ+ ለቂጣ+..ማብሰያ የሚያገለግል ጠፍጣፋና ክብ የሆነ የቤት እቃ::

**የምጣድ ሸሮ** ስ ሽሮን ከዘይትና ከሌሎች ቅመሞች ጋር አዋህዶ በምጣድ በማብሰል የሚዘጋጅ እንደ ወጥ የሚያገለግል የእንጀራ ማባያ::

**ተጣደ** ግ 1. እሳት ላይ ተደረገ(ድስት+ ምጣድ+...)::2. እሳት ዳር ተቀመጠ+ ተወዘፈ (ሰው)::

**ጣዲቅ** "ፀደቀ" ስር "ፀዲቅ"ን ተመ.

**ጣጋ** ቅ ከሲታ+ ከሳሳ::

**ጣጣ** ስ 1. ችግር፤ ውጣውረድ፥ ውስብስብነት። 2. መዘዝ።

**ጣጣ ገባ** መከራ፥ ችግር ውስጥ ገባ።

**ጣጠኛ** ቅ መከራው፥ ችግሩ የበዛ። 2. መዘኛ።

***ጣጣ**

**ጣጣቴ** ስ 1. ከህመም ያድናል እየተባለ በሽተኛን በጋለ ብረት የመተኮስ ድርጊት። 2. ለፍላፊ። 3. የሚንጣጣ ድምፅ።

**ተንጣጣ** ግ 1.እየተቆላ ያለ ተልባ ወይም ግሽላ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ። 2. ለፈለፈ።

**አንጣጣ** ግ 1. የሚንጣጣ ተከታታይ ድምፅ አሰማ ወይም እንዲሰማ አደረገ። 2.አስለፈለፈ፥ አስቀባጠረ።

**ጣጣለ** "ጣለ" ስር ተመ.

**ጣጣቴ** "*ጣጣ" ስር ተመ.

**ጣፈ** ግ በተቀደደው ልብስ ላይ ሌላ ጨርቅ ደርቦ ሰፋ፥ ጠቀመ፥ ደረተ። 2. አላከከ። *ጥፋቱን በእኔ ላይ ጣፈብኝ።*

**መጣፊያ** ስ በተቀደደ ጨርቅ ላይ ተለጥፎ የሚሰፋ እራፊ ወይም ቁራጭ ጨርቅ።

**ተጣፈ** ግ ተደረተ፥ቀዳዳው እራፊ ጨርቅ ተደርቦበት ተሰፋ።

**ጣፈጠ** ግ ጣመ፥ ጥሩ ጣእም አገኘ (ምግብ፥ መጠጥ)።

**ጣፋጭ** ቅ 1. የሚጥም፥ ጥሩ ጣእም ያለው፥ የሚጣፍጥ። 2. ስኳርነት ያለው።

**አጣፈጠ** ግ 1. አጣመ፥ ጥሩ ጣእም እንዲኖረው አደረገ (ምግብን፥ መጠጥን)። 2. አሳመረ፥ አስዋበ (ነገርን)።

**ማጣፈጫ** ስ (ምግብን፥ መጠጥን) የሚያጣፍጥ፥ ጥሩ ጣእም እንዲሰጥ የሚያደርግ ቅመም ወይም ሌላ ነገር።

**ጣፊያ** ስ በሆድ ውስጥ በግራ በኩል በላይኛው ክፍል የሚገኝ፥ ሐቆር ያለ ቀይ መልክና ሞለል ያለ ቅርፅ ያለው፥ ደምን በመስራት ለማጠራቀምና ለማጣራት የሚጠቅም የሰውነት ክፍል።

**ጣፉ** ስ ከወርቅ፥ ከብር፥... የሚሰራ የጋሻ ጌጥ።

**ጣፋጭ** "ጣፈጠ" ስር ተመ.

**ጣፎርዱ** ቅ (ስድብ) ጋጠወጥ፥ ባለጌ።

**ጤ** የ "ጠ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ጤሰ** "ጨሰ" ን ተመ.

**ጤቅ** ስ ድብዳብ፥ መደላድል (ጭነቱ እንዳይጎዳው በጋማ ከብት ጀርባ ላይ የሚደረግ)።

***ጤነ**

**ተጤነ** ግ ተመረመረ፥ ልብ ተባለ፥ ተስተዋለ።

**አጤነ** ግ መረመረ፥ አስተዋለ፥ ልብ አደረገ።

**ጤና** ስ ደህንነት፥ ከበሽታ ነፃ መሆን።

**ጤና ሰጠ** ሰላም ሰጠ።

**ጤና ነሳው** 1. ሰላም እንዳያገኝ አደረገው፥ አወከው። 2. ህመምተኛ ወይም ታማሚ ሆነ።

**ጤና አገኘ** ታሞ የነበረው ዳነ፥ ጤነኛ ሆነ።

**ጤና ይስጥልኝ** ሰዎች በሚገናኙበት አንዳንዴም በሚለያዩበት ጊዜ የሚለዋወጡት የሰላምታ ቃል።

**ጤና መኮንን** ስ በህክምና ትምህርት የሰለጠነ ባለሙያ።

**[የ]ጤና ረዳት** ስ የተወሰነ የህክምና እርዳታ አሰጣጥ ትምህርት የተማረ የጤና ባለሙያ።

**ጤና ቢስ** ቅ 1. አዘውትሮ የሚያመው፥ በሽተኛ። 2. ነገረኛ፥ ጠበኛ።

**ጤና ጣቢያ** ስ ደረጃው ከሆስፒታል አነስ የሚልና መለስተኛ የህክምና እርዳታ የሚሰጥበት የህክምና ተቋም።

**ጤነኛ** ቅ 1. የማያመው፥ ህመም የሌለው። ጤናማም ይባላል።2. እንከን፥ ችግር፥... የሌለበት።

**ጤናማ** "ጤነኛ"ን ተመ.

**ጤናዳም(ጤና አዳም)** ስ ከአገር ባህል መድሃኒት ጋር እየተቀመመ ወይም ብቻውን ለመድሃኒትነት ያገለግላል የሚባልና ጥሩ ሽታ ያለው ተክል።

**ጤንነት** ስ ደህንነት፤ የሰውነት፥ የአካል ጤናማ መሆን።

**ጤዛ** ስ በሳርና በቅጠል ላይ ቧት ቧት ወይም ዝናብ ከዘነበ በ ሗላ ተንቆርዞ የሚታይ የውሃ ጠብታ።

**ጤዛ ጣለ** በሳርና በቅጠል ላይ የውሃ ጠብታ ተንቆረዘዘ።

**ጤዛ ረገፈ** ጤዛው ደረቀ።

**ጤፍ** ስ ተፈጭቶና በቀጭኑ ተቦክቶ ሲጋገር እንጀራ የሚሆን ትናንሽ ፍሬዎች ያሉት የእህል አይነት፤ ፍሬውም ጤፍ ይባላል።

**ጥ** የ "ጠ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**ጥለት**[1] ስ በነጠላ፥ በቀሚስ፥ በጋቢ፥... ዳር ላይ የሚሰራ፥ የተለያየ ቀለም ያለው ክር፤ እዳይት።

**ጥለት ጣለ** በሸማ፥ በኩታ፥... ዳር ላይ ጥለት ሰራ፤ በጥለት አስጌጠ።

**ጥለት**[2] "ጣለ" ስር ተመ.

**ጥለኛ** "ጠላ²" ስር ተመ.

**ጥላ** "*ጠላ" ስር ተመ.

**ጥላሸት(ጠለሸት፥ ጥላት)** ስ በእሳት ጢስ ምክንያት የሚፈጠር ጥቁር ቆሻሻ፥ ጥቀርሻ።

**ጥላሸት ለበሰ** ፊቱ በጣም ጠቆረ (በሃዘን፥ በፀሃይ፥ በድንጋጤ፥... የተነሳ)።

**ጥላሸት ቀባ** ስም አጠፋ ፣ አዋረደ።

**ጥላቻ** "ጠላ²" ስር ተመ.

**ጥላይ** "ጠለለ" ስር ተመ.

**ጥል** "ጠላ²" ስር ተመ.

**ጥልማሞት** "ፅልመት" ስር "ፅልማሞት"ን ተመ.

**ጥልምያኮስ**"ፅልመት"ስር "ፅልመያኮስ"ን ተመ.

**ጥልቀት** "ጠለቀ¹ " ስር ተመ.

**ጥልቅ** ዝ.ከ.

**ጥልቆ** ስ አነስተኛ መጥረቢያ።

**ጥልጣል** ስ ከቁጠማ የሚሰራ የቤት ወለል ምንጣፍ።

**ጥልፊያ** "ጠለፈ" ስር ተመ.

**ጥልፍ** ዝ.ከ.

**ጥልፍልፍ** ዝ.ከ.

**ጥሎሽ** "ጣለ" ስር ተመ.

**ጥመት** " ጠመመ" ስር ተመ.

**ጥሙር** "ጠሞረ" ስር ተመ.

**ጥማት** "ጠማ" ስር ተመ.

**ጥማድ** "ጠመደ¹" ስር ተመ.

**ጥም** "ጠማ" ስር "ጥማት"ን ተመ.

**ጥምልምል** "*ጠመለመለ" ስር ተመ.

**ጥምር** "*ጠመረ" ስር ተመ.

**ጥምቀት** "ጠመቀ" ስር ተመ.

**ጥምቢራ (ጥንቢራ)**

**ጥምቢራው ዞሯል** በጣም ሰክሯል።

**ጥምብ** "ጠነባ" ስር ተመ.

**ጥምዝ** "ጠመዘዘ" ስር ተመ.

**ጥምጣም** "ጠመጠመ" ስር ተመ.

**ጥምጥም** ዝ.ከ.

**ጥሞና** "ፅሞና"ን ተመ.

**ጥረሾ** ስ ሳይቦካ (ኩፍ ሳይል) የሚጋገር ስስና ደረቅ የሆነ የገብስ ቂጣ።

**ጥረት** "ጣረ" ስር ተመ.

**ጥሩ** "ጠራ²" ስር ተመ.

**ጥሩምባ** ስ 1. ከነሃስ ወይም ከሌላ ተመሳሳይ ነገር የሚሰራ፥ ከፍ ያለ ድምፅ የሚያወጣና በትንፋሽ የሚሰራ የሙዚቃ መሳሪያ (ለእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)። 2. የመኪና ጥሩምባ።3. (ዘይ.) ወሬኛ፥ ለፍላፊ።

**ጥሩምባ ነፊ** ስ ጥሩምባን በመጠቀም የሙዚቃ ድምፅ የሚያሰማ ወይም የጥሪ መልእክትየሚያስተላልፍ ሰው።

**ጥሩር** ስ በቀድሞ ጊዜ ወታደሮች ጦርነት ላይ ሲሰማሩ ለመከላከያነት የሚለብሱት ከብረት የሚሰራ የጦር ልብስ።



ጥሩር

**ጥሪ** "ጠራ¹" ስር ተመ.

**ጥሪት** ስ አንጡራ ሃብት፥ ንብረት።

**ጥራር** ስ ከሸንበቆ ወይም ከቀርከሃ ወይም ከሃረግ፥... የሚሰራ አገልግል፥ መሶብ፥ ቅረጫት።

**ጥራቢ** "ጠረበ" ስር ተመ.

**ጥራት** "ጠራ²" ስር ተመ.

**ጥራዝ** "ጠረዘ" ስር ተመ.

**ጥራጊ** "ጠረገ" ስር ተመ.

**ጥሬ** ስ 1. ያልላመ፥ ያልደቀቀ፥ ያልተፈጨ እህል። 2. ያልበሰለ፥ ያልሞከከ፥ ያልጎመራ (ፍራፍሬ)። 3. ቆሎ፥ ንፍሮ። *የቆሎ ተማሪ ጥሬ በልቶ፥ ውሃ ጠጥቶ ነው የሚማረው።* 4.በእሳት ያልበሰለ ወይም ያልተቀቀለ (እህል፥ ስጋ)። 5. (ዘይ.) ነፍስ ያላወቀ፥ ማስተዋል የሚያንሰው።6. ከሚፈለገው ደረጃ ያልደረሰ፥ ገና የሆነ።*ጉዳዩ ገና ጥሬ ነው።*

**ጥሬ ነው** 1. አልተጎዳም፥ አላለቀም (ልብስ)። 2. አልበሰለም፥ ለመበላት አልደረሰም። 3. አልሰለጠነም(ለሰው)።

**ጥሬ ስጋውን በሉት** አሙት።

**ጥሬና ብስል** ቅ የጥሩና የመጥፎ፥ የሚረባና የማይረባ ነገር ቅልቅል።

**ጥራጥሬ** ስ እንደ ባቄላ፥ አተር፥ምስር፥... ያለ የእህል አይነት የወል መጠሪያ።

**ጥሬ ካብ** ስ ጭቃ፥ ኖራ፥ ስሚንቶ ያልገባበት፥ በድንጋይ ብቻ የተሰራ ካብ።

**ጥሬ ዘር** ስ (ሰዋ.) ከግሳዊ ቃል በእርባታ ዘዴ የሚፈጠርና በስምነት ሊያገለግል የሚችል ውልድ ቃል (ለምሳሌ መነነ ብሎ ምናኔ፣ ሰቀለ ብሎ መስቀል፣ ለፋ ብሎ ልፋት፣ ዳነ ብሎ መድሃኒት፥... የመሳሰለው ሁሉ)።

**ጥሬ ገንዘብ** ስ ብር ብቻ (እቃን ወይም ሌላ ንብረትን ሳይጨምር)።


**ጥሬ ጥጥ** ስ ያልተፈለቀቀ ወይም ፍሬው ያልወጣ ጥጥ።

**ጥሬ ጨው** ስ ያልተፈጨ ጨው፤ አሸቦ።

**ጥሬ ፈጅ** ስ ቡላ መልክ ያለውና ብዙ ሆኖ ባንድነት የሚሄድ፥ እህል የሚበላ የወፍ አይነት፤ ጨረባ።

**ጥር** ስ ከታህሳስ ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ አምስተኛ ወር ስም።

**ጥርስ** ስ 1. በሰውና በእንስሳት አፍ ውስጥ የሚገኝ፥ ለምግብ መፍጫ የሚያገለግል፥ ነጭና ጠንካራ የሆነ የሰውነት ክፍል። 2. የማጭድ ወይም የመጋዝ ዘርዛራ የሆነው ስለት። 3. እባጭ ወይም ብጉንጅ በሚፈርጥበት ጊዜ ከውስጡ የሚወጣ ጠጠር ያለ መግል። 4. እንቅስቃሴን ከአንድ አካል ወደ ሌላ ለማስተላለፍ፥ ፍጥነትን ለመቆጣጠር፥ አቅጣጫን ለመቀያየር፥... የሚያገለግልና በዘርዛራው የተከረከረ ጠርዝ ያለው የሞተር ወይም የማሽን፥... ክፍል።



ጥርስ

**በጥርሱ ሸኘ** በፈገግታ ደለለ፥ አታለለ፥ ሸነገለ።

**ጥርሱ ረገፈ** ጥርሱ ወለቀ (ብዙውን ጊዜ ከአንድ በላይ ጥርስ)።

**ጥርሱን ቀረጠመ** ጥርሱን አፋጨ፥ አንቀራጨጨ (በእንቅልፍ ጊዜ)።

**ጥርሱን ሸርፏል/ ስብሯል** እድሜው ከፍ በማለቱ በፊት የነበረው ጥርስ ወልቆ ሌላ አብቅሏል (እንደ በቅሎ፥ ፈረስ፥... ያለ እንስሳ)።

**ጥርስ አወጣ** 1. ጥርስ አበቀለ። 2. ሳለ፥ ሞረደ (መጋዝን፥ ማጭድን፥...)።

**ጥርሱን ነከሰ** ዛተ፥ ቂም ያዘ።

**ጥርስ ገባ** ተጠላ፥ ተጠመደ።

**የጥርስ ሃኪም** ስ በተለይ በጥርስ ህክምና የሰለጠነ ባለሙያ።

**የጥርስ ሳሙና** ስ ጥርስን ለማፅዳት የሚያገለግል ሳሙና።

**የጥርስ ብሩሽ** ስ ጥርስን ለማፅዳት የሚያገለግል ብሩሽ።

**ጥርስ በረዶ** ቅ ጥርሱ በጣም ነጭ የሆነ።

**ጥርስ ፍንጭት** ቅ በፊት ጥርሶቹ መካከል ክፍት ቦታ ያለው፤ ፍንጭትም ይባላል።

**ጥርሳም** ቅ 1. ጥርሱ ወደ ውጭ የወጣ፤ ገጣጣ።2.መሳቅ የሚያበዛ።

**ጥርቃሞ** "*ጠረቀመ" ስር ተመ.

**ጥርቅም** ዝ.ከ.

**ጥርቅምቅም** ዝ.ከ.

**ጥርብ** "ጠረበ" ስር ተመ.

**ጥርኝ**[1] ስ ገላዋ ዝባድ በመባል የሚታወቀውንና ጥሩ መአዛ ያለውን ኩክ መሳይ ወዝ የሚያመነጭ እንደ ድመት ያለች የአውሬ አይነት፤ ከአካሏ የሚመነጨውም ኩክ መሳይ ወዝ ጥርኝ ወይም ዝባድ ተብሎ ይጠራል (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ጥርኝ ፈረስ** ስ መልኩ ግራጫ የሆነ ፈረስ።

**ጥርኝ**[2] ቅ የእፍኝ ግማሽ፤በአንድ የውስጥ እጅ ሊያዝ የሚቻል መጠን። ኣንድ ጥርኝ ቆሎ።

**ጥርዝ** "ጠረዘ" ስር ተመ.

**ጥርጊያ** "ጠረገ" ስር ተመ.

**ጥርጣሪ** "ጠረጠረ[2]" ስር ተመ.

**ጥርጣሬ** "ጠረጠረ[1]" ስር ተመ.

**ጥርጥር** ዝ.ከ.

**ጥርጥስ** " ጠረጠሰ" ስር ተመ.

**ጥስቅ** "ጠሰቀ" ስር ተመ.

**ጥሻ(ጢሻ)** ስ ዳዋ፤ ጥቅጥቅ ያለ ሳርና ቁጥቋጦ።

**ጥቀርሻ** ስ ጪስ በሚጨስበት ቤት ጣሪያ ወይም ኮርኒስ ላይ የሚገኝ የጪስ ብናኝ ጥርቅም፥ ጥላሸት።

**ጥቁራት** "ጠቆረ" ስር ተመ.

**ጥቁሬ** ዝ.ከ.

**ጥቁር** ዝ.ከ.

**ጥቂት** ቅ በጣም ትንሽ፤ መጠኑ ወይም ቁጥሩ አነስተኛ የሆነ።

**ጥቃተኛ** "*ጠቃ" ስር ተመ.

**ጥቃት** ዝ.ከ.

**ጥቅለላ** "ጠቀለለ" ስር ተመ.

**ጥቅል** ዝ.ከ.

**ጥቅም** "ጠቀመ" ስር ተመ.

**ጥቅምት** ስ ከመስከረም ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ ሁለተኛ ወር ስም።

**ጥቅስ** "ጠቀሰ" ስር ተመ.

**ጥቅሻ** ዝ.ከ.

**ጥቅጥቅ** "ጠቀጠቀ" ስር ተመ.

**ጥቆማ** "ጠቆመ" ስር ተመ.

**ጥበቃ** "ጠበቀ[1]" ስር ተመ.


**ጥበበኛ** "*ጠበበ" ስር ተመ.

**ጥበብ** ዝ.ከ.

**ጥበት** "ጠበበ" ስር ተመ.

**ጥቢ** "ጠባ[2]" ስር ተመ.

**ጥቢኛ(ጢብኛ)** ስ ሙልሙል ጸቦ፥ ሀብበት::
**ጥባት** "ጠባ$^{2}$" ስር ተመ.
**ጥብርር** "*ጠበረረ" ስር "ጠብራራ"ን ተመ.
**ጥብስ** "ጠበሰ" ስር ተመ.
**ጥብቅ$^{1}$** "ጠበቀ$^{2}$" ስር ተመ.
**ጥብቅ$^{2}$** "ጠበቀ$^{1}$" ስር ተመ.
**ጥብቅና** "*ጠበቀ$^{2}$" ስር ተመ.
**ጥብቆ** ስ ጠበብ ብሎ የተሰፋ የልጅ ልብስ::
**ጥብጠባ** "ጠበጠበ" ስር ተመ.
**ጥብጣብ** ስ 1. ከፈትል ወይም ከተለያየ ጥለት ተጎንጉኖ የሚሰራ የሱሪ መታጠቂያ፥ ሽምቀቆ:: 2. በካባ ላይ በስተፊት በኩል በግራና በቀኝ የሚወርድ ጌጥ 3. እንደ መቀነት ያለ ቀጭንና ረጅም ጨርቅ:: *ሉዊሱ መንገድ በተመረቀ ጊዜ ጥብጣቡን የቆረጡት ስራ አስኪያጁ ናቸው::*
**ጥብጥባት** "ጠበጠበ" ስር ተመ.
**ጥኑ** "ጠና" ስር "ፅኑ"ን ተመ.
**ጥና** "ፅንሃህ" ን ተመ.
**ጥናት$^{1}$** "ጠና" ስር "ፅናት"ን ተመ.
**ጥናት$^{2}$** "*ጠና" ስር ተመ.
**ጥንስስ** "ጠነሰሰ$^{1}$" ስር ተመ.
**ጥንቁቅ** "ጠነቀቀ" ስር "ጠንቃቃ"ን ተመ.
**ጥንቃቄ** "ጠነቀቀ" ስር ተመ.
**ጥንቅሽ** ስ 1. መልኩ እንደ በቆሎ አገዳ ያለ ሆኖ ቀጠን ቀጠን የሚል ሸንኮራ፣ ጥንቅሽ አገዳ:: 2. አገዳው እንደ ሸንኮራ ጣፋጭነት ያለው የማሽላ አይነት::
**ጥንቆላ** "ጠነቆለ" ስር ተመ.
**ጥንቢራ** "ጥምቢራ"ን ተመ.
**ጥንባት** "ጠነባ" ስር ተመ.
**ጥንብ** ዝ.ከ.
**ጥንታዊ** "ጥንት" ስር ተመ.
**ጥንት** ተው.ግ ድሮ፥ ቀድሞ::
**ጥንተ አካል** ስ በቀድሞ ዘመን ወይም ከረጅም ጊዜ በፊት የነበረ የሰው ወይም የአውሬ ወይም የሌላ ነገር አካል ክፍል፣ ቅሪት::
**ጥንታዊ** ቅ የድሮ፥ በቀድሞ ዘመን የነበረ ወይም ከድሮ፥ ከጥንት ጀምሮ የነበረ፥ ያለ::
**ጥንቸል** ስ የፍየል ግልገል የምታክል፥ ስትሄድ ጡብ ጡብ እያለች የምትዘል፥ አጭር ጅራትና ረጅም ጆሮ ያላት እንስሳ(ስእሉን የጱር እንስሳ ስር)::
**ጥንካሬ** "ጠነከረ" ስር ተመ.
**ጥንዚዛ** ስ ሲበር ጥዝ ጥዝ የሚል ድምፅ የሚያሰማና ጥቁር ወይም አረንጓዴ የሆነ በራሪ ነፍሳት::



ጥንዚዛ

**ጥንዚዛ የመሰለ** በጣም ጥቁር የሆነ::
**ጥንጉት** "ጥንጁት" ን ተመ.
**ጥንድ** ቅ ሁለት፥ መንታነት ያለው::
**በጥንድ በጥንድ** ሁለት ሁለት በመሆን::
**ጥንድ በሬ** በአንድነት እርሻ ላይ የሚሰማሩ፥ የተቀናጁ ሁለት በሬዎች::
**ጥንድ ጫማ** አንድ ላይ የሚደረግ የሁለት እግር ጫማ::
**ጥንጁት (ጥንጉት)** ስ በወይና ደጋና በቆላ የሚበቅል፥ መልኩ ነጣ ያለ ሆኖ እሸሁ ያለው፥ ለጠላ እቃ ማጠኛ፥... የሚያገለግል የእፅዋት አይነት::
**ጥንግ** "*ጠነገ" ስር ተመ.
**ጥንጣን** "ጠነጠነ$^{1}$" ስር ተመ.
**ጥንጥን** "*ጠነጠነ" ስር ተመ.
**ጥንፍ** "ጠንፍ" ስር ተመ.
**ጥዋ** "ፅዋ"ን ተመ.
**ጥዋት** "ጧት"ን ተመ.
**ጥውር** "ጠረ" ስር ተመ.
**ጥዝ**
**ጥዝ አለ** ግ ንብ ወይም ጥንዚዛ ሲጮህ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ::
**ጥዝጣዜ** "ጠዘጠዘ" ስር ተመ..
**ጥዩፍ** "*ፀየፈ" ስር "ፅዩፍ"ን ተመ.
**ጥያቄ** "ጠየቀ" ስር ተመ.
**ጥይት** ስ ውስጡ በባሩድየተሞላና አረር የተገጠመለት ቀለሀ (በጠመንጃ፥ በሽጉጥ ተደርጎ ከምሱሩ ሲወጋ ተቀጣጥሎ የሚፈነዳ ወይም የሚተኮስ)::




**የጥይት ራት ሆነ** በጥይት ተመትቶ ሞተ::
**ጥይት ነው** ጎበዝ፥ፈጣን፥ቀልጣፋ ነው::
**ጥድ(ፅድ)** ስ እንጨቱ ጠንካራ የሆነ ትልቅ የዛፍ አይነት::
**ጥድፊያ** "*ጠደፈ" ስር ተመ.
**ጥዶ ዘለል** "ጣደ" ስር ተመ.

**ጥጃ** ስ ከእምቦሳ ከፍ የሚልና ሳር መብላት፣ ውሃ መጠጣት የጀመረ የላም ልጅ።

**ጥጃ ሆድ** ቅ ሆዱ ቀዝር ያለ።

**ጥገት** ስ ጥጃ ያላት፣ የምታጠባና የምትታለብ ላም።

**ጥገና** "ጠገነ" ስር ተመ

**ጥገኛ** "*ጠጋ" ስር ተመ.

**ጥጉብ** "ጠገበ" ስር ተመ.

**ጥጋበኛ** ዝ.ከ.

**ጋብ** ዝ.ከ.

**ጥጋት**[1] ስ ያልታረሰ ወይም እጻሪ የሆነ መሬት።

**ጥጋት**[2] ስ ጥግ።

**ጥጋጥግ** "*ጠጋ" ስር ተመ.

**ጥግ** ዝ.ከ

**ጥግን** "ጠገነ" ስር ተመ.

**ጥጥ** ስ 1. በቆላ አካባቢ የሚበቅል፣ እምቡጡ ሲፈነዳ በውስጡ ለልብስና ለሌላም አገልግሎት የሚውል ለስላሳ የሆነ ነጭ ጭገር የሚገኝበት ተክል። 2. ከጥጥ ተክል የሚገኝ ተባዝቶና ተፈትሎ ድርናማግ የሚሆን ልስልስ ጭገር፣ ፍንድ።

**[የ] ጥጥ ፍሬ (ጥፍጥሬ)** ስ በጥጥ ውስጥ የሚገኝ ጥቁር ፍሬ።

**የጥጥ ፍንድ** ስ ሊለቀም የደረሰና እምቡጡ የፈነዳ ጥጥ።

**ጥጥር** "ጠጠረ" ስር ተመ.

**ጥፉ** "ጠፋ[1]" ስር ተመ.

**ጥፊ** "ጠፋ[2]" ስር ተመ.

**ጥፉተኛ** "ጠፋ[1]" ስር ተመ.

**ጥፉት** ዝ.ከ.

**ጥፌ**[1] ስ ቅጠሉ ጫት የሚመስልና የእከክ ወይም የችፌ መድሃኒት ይሆናል የሚባል፣ ግንዱ ለእርፍና ለሞፈር ስራ የሚያገለግል የዛፍ አይነት።

**ጥፌ**[2] "ጠፋ[1] " ስር ተመ.

**ጥፍሪንዶ** "ጥፍርንዶ" ን ተመ

**ጥፍር** ስ በእጅና በእግር ጣት ጫፍ ላይ የሚበቅል ጠንካራ የሆነ የአካል ክፍል።

**የጥፍር ሞረድ** ስ ለጥፍር መሞረጃና ማለስለሻ የሚያገለግል አነስተኛና ሸካራ ብረት።

**የጥፍር ቀለም** ስ ሴቶች ጥፍራቸውን የሚያስውቡበት ቀለም።

**ጥፍረ መጥምጥ** ስ ጥፍር ላይ በሚደርስ አደጋ ምክንያት የሚመጣና ጥፍርን የሚያወልቅ ወይም የሚያጠቁር ህመም።

**ጥፍራም** ቅ (ስድብ) ባለጌ፣ ስድ።

**ጥፍርንዶ(ጥፍሪንዶ)** ስ ወተት የሚመስል ፈሳሽ ነገር የሚወጣው፣ ልጡ ለቁግ (ለጅራፍ ጫፍ) የሚሆንና እንደ ጥጥ ያሉ አበባዎች የሚያወጣ የእፅዋት አይነት።

**ጥፍጥሬ** "ጥጥ" ስር "ጥጥፍሬ"ን ተመ.

**ጥፍጥፍ** "ጠፈጠፈ" ስር ተመ.

**ጠ** የ "ጠ" ፊደል ሳብእ ዘር።

***ጦለ**

**ተጦለ** ግ ገርዱና ገለባው ከፍሬው (ከምርቱ) ተለየ።

**አጦለ** ግ በማጦያ ገርድን፣ ገለባን ከፍሬው ለየ።

**ማጦያ** ስ ከስንደዶ ወይም ከጭራንፎ እንደ መጥረጊያ ሆኖ የሚሰራ ገርድንና ገለባን ከፍሬው ለመለየት የሚያገለግል እቃ።

***ጦለጦለ**

**ጦልጧላ** ቅ (ስድብ) ከውካዋ፣ ዘዋሪ።

**ተንጦለጦለ** ግ ተንከወከወ፣ አርፎ አልቀመጥ አለ፣ እዚያም እዚያም ሄደ።

**አንጦለጦለ** ግ አንከወከወ፣ አዞረ።

**ጦሊት** ስ ሴቶች በአንገታቸው ላይ የሚደርቧትና በሁለቱም ጫፎች በኩል ጥለት ያላት አንድ አርብ ነጠላ።

**ጦልጧላ** "*ጦለጦለ" ስር ተመ.

**ጦሎታ** ስ ሲገርፉበት ወይም ሲያወናጭፉት ድምፅ የሚያሰማው ወይም የሚጮህው የጅራፍ ጫፍ፤ ቁግ።

**ጦመ** "ፆመ"ን ተመ.

**ጦማር** ስ ደብዳቤ፣ በፅሁፍ የሰፈረ መልእክት።

**ጦረ (ጠወረ)** ግ ያረጀን ወይም የደከመን ሰው ረዳ፣ አገዘ፣ ተንከባከበ (በምግብ፣በልብስ፣ በመጠለያና በመሳሰሉት)።

**ጡረታ** ስ 1. የመንግስት ወይም የግል ድርጅት ሰራተኛ በአገልግሎት ላይ እያለ በደንቡ መሰረት የተወሰነ ገንዘብ በየወሩ በተቀማጭ መልክ ከደመወዙ እየተቀነሰ የሚቀመጥበትና አቅሙ ሲደክም ወይም የእድሜ ገደቡ ሲደርስ ከስራ ውጪ ሆኖ ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ የመተዳደሪያ አበል የሚሰጥበት ሁኔታ። 2. ሽማግሌን ወይም አቅመ ደካማን በኑሮ የመርዳት ተግባር።

**ጡረታ ወጣ** የተወሰነው የእድሜው ገደብ በመድረሱ ወይም በህመም ምክንያት የነበረበትን የስራ ቦታ ለቀቀ፤ ከስራ ተሰናበተ።

**የጡረታ አበል** ስ በጡረታ ላይ ላለ ሰው የሚከፈል ገንዘብ።

**ጡረተኛ** ስ የእድሜው ገደብ በመድረሱ÷ ወይም በሌላ ምክንያት ስራ ያቆመ ወይም ከስራ የተሰናበተ ሰው።


**ጥውር** ቅ ኑሮው በቤተሰብ÷ በወዳጅ÷...የሚረዳ፣ ተጠዋሪ።

**ጧሪ** ቅ በሽምግልና ወይም በእርጅና ጊዜ የሚረዳ÷ የሚያግዝ÷ የሚንከባከብ።

**ተጦረ(ተጠወረ)** ግ በሽምግልና ወይም በእርጅና ጊዜው እየተረዳ ኖረ።

**ተጧሪ(ተጠዋሪ)** ቅ እየተረዳ የሚኖር።

**ጦር** ስ ከብረት የሚሰራና በሁለቱም ጎኑ ስለታም የሆነ ሹል ጫፍ ያለው ለመውጊያ የሚያገለግል መሳሪያ። 2. በጦርነት ጊዜ የሚሰለፍ ሰራዊት÷ወታደር÷...። *ጦር መጣ።*



ጦር

**እንደጦር ይፈራል** ከመጠን በላይ ይፈራል። *ሰውዬውን እንደ ጦር ይፈራዋል።*

**ጦሩ ተፈታ** ተዋጊው ሰራዊት ተሸነፈ÷ ድል ሆነ።

**ጦር ሰበቀ** ለመወርወር ወይም ለመውጋት ጦሩን ነቀነቀ÷ ተዘጋጀ።

**[የ] ጦር ሃይሎች** ስ የምድር ጦርን÷ የአየር ሃይልን÷...የመሳሰሉ የተለያዩ የጦር ሰራዊት ክፍሎችን የሚያጠቃልል መጠሪያ።

**የጦር ልምምድ** ስ ብቃትን ከፍ ለማድረግ የሚካሄድ የውጊያ ልምምድ።

**የጦር መሪ** ስ በጦርነት ላይ የተሰለፈ ተዋጊ ቡድንን የሚመራ የበላይ አዛዥ፣ አዝማች።

**የጧር መሳሪያ** ስ የሞት ወይም የማቁሰል አደጋ ወይም ሌላ ጥፋት ሊያደርስ የሚችል እንደ ጦር÷ ሽጉጥ÷ ቦምብ÷... ያለ መሳሪያ።

**የጦር መኮንን** ስ ከምክትል መቶ አለቃ ጀምሮ ከፍተኛ ማእርግ ያለው የጦር ሰራዊት ባልደረባ።

**የጦር ምርኮኛ** ስ በጦርነት ጊዜ ተማርኮ የተያዘ ተዋጊ።

**[የ] ጦር ሰራዊት** ስ የአንድን ሃገር ዳር ድንበር የሚጠብቅና ሉአላዊነትን የሚያስከብር ወታደራዊ ሃይል።

**የጦር አማካሪ** ስ በጦር ሃይሎች ውስጥ ልዩ ልዩ ምክሮችና አስተያየቶችን የሚሰጥ የሰለጠነ ወይም ልምድ ያለው የጦር መኮንን።

**የጦር አበጋዝ** ስ የጦር መሪ።

**የጦር አካዴሚ** ስ ከፍ ያለ ወታደራዊ ሙያ የሚቀሰምበት የትምህርት ተቋም።

**የጦር አዛዥ** ስ የጦር ሃይል ክፍልን ለማንቀሳቀስ ወይም ለማዝመት የሚችልና ትእዛዝ የሚሰጥ ከፍተኛ ባለስልጣን።

**የጦር አዝማች** ስ የጦር መሪ።

**የጦር ካሳ** ስ በጦርነት ላይ ለደረሰ ጉዳት አጥፊው ወገን ለተጎጂው የሚከፍለው ካሳ።

**የጦር ወንጀለኛ** ስ በጦርነት ጊዜ እስረኞችን ያላግባብ የማሰቃየት÷ ሰላማዊ ሰዎችን የመጨፍጨፍና የመሳሰሉትን ኢሰብአዊ ድርጊቶች የፈፀመ ሰው።

**የጦር ገበሬ** ስ ሃይለኛ ተዋጊ።

**የጦር ጉዳተኛ** ስ በጦርነት ላይ የመቁሰል አደጋ የደረሰበት ወታደር ወይም ተዋጊ።

**ጦር ሜዳ** ስ ጦርነት የተደረገበት ወይም የሚካሄድበት ቦታ።

**የጦር ሜዳ መነፅር** ስ በጦርነት ጊዜ የሚገለገሉበት ሩቁን አቅርቦ የሚያሳይ መነፅር።

**ጦር ሰፈር** ስ ወታደር ወይም ሰራዊት የሰፈረበት ቦታ፣ ካምፕ።

.**ጦር ውርወራ** ስ ከተወሰነው ቦታ ላይ በመሆን ጦርን አርቆ ለመወርወርና አሸናፊ ለመሆን የሚደረግ ስፖርታዊ ውድድር።

**ጦር ግንባር** ስ የውጊያ÷ የፍልሚያ ቦታ፣ የጦርነት መስመር።

**ጦር ጠማሽ** ቅ ጦርነት ናፋቂ ወይም ፈላጊ።

**ጦረኛ** ቅ 1. የጦርነት ዘዴ ወይም ስልት አዋቂ፣ የጦር ጀግና። 2. ጦር ጠማሽ። ✓

**ጦርነት** ስ 1. በተቃራኒ ወገን ወይም ሃገሮች መካከል የሚደረግ የመሳሪያ ውጊያ÷ ፍልሚያ። 2. ትግል÷ ግብግብ። *እቃ ለመግዛት ያለው ጦርነት ከባድ ነው።*

**የጦርነት ደመና አንዣቧል** ጦርነት ሊጀመር ወይም ሊካሄድ ተቃርቧል።

**ጦርነት አወጀ** ጦርነት እንደሚጀመር ወይም እንደሚካሄድ በይፋ ተናገረ።

**ጦርነት ከፈተ** ውጊያ ጀመረ።

**ጦስ** ስ 1. ሰበብ÷ ምክንያት። 2. ችግር÷ መዘዝ÷ መከራ።

**ጦሰኛ** ቅ መዘዘኛ።

**ጦስኝ** ስ በደጋና በወይና ደጋ የሚበቅል÷ ጥሩ ሽታ ያለውና ለቅመምነት የሚያገለግል አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

**ጦሽ**

**ጦሽ አለ** ግ 1. እርጥብ እንጨት ሲነድ

የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ። 2. ፈነዳ። 3. በሃይል ሳቀ ወይም አለቀሰ።

**ጦሽ አደረገ** ግ 1. አፈነዳ፥ አጮሀ። 2. በሃይል አሳቀ ወይም አስለቀሰ።

**ተንጦሸጦሸ** ግ ተንጣጣ።

**አንጦሸጦሸ** ግ አንጣጣ (በመቁላት፥ በመጥበስ፥ በመተኮስ፥..)።

***ጦነጦነ**

**ጦንጧና** ቅ ከውካዋ፥ ጦልጧላ፥ ዘዋሪ።

**ጡንጡን አለ** ግ ከውከው፥ ጡልጡል አለ።

**አጦነጦነ** ግ ወዲያ ወዲህ ተንከወከወ፣ ጡልጡል አለ።

**ጦዘ** ግ ከረረ፥ ተጠመዘዘ (ክር)። 2. (ዘይ.) ተጋጋለ፥ ሞቀ።

**ጡዘት** ስ በልብወለድ ፅሁፍ፥ በፊልም፥... ውስጥ የታሪኩ ሂደት ከፍተኛ ቦታ የሚደርስበትና ስሜት የሚይዝበት፥ በስተመጨረሻ አካባቢ ያለው የድርሰቱ አካል።

**አጦዘ** ግ 1.አከረረ፥ጠመዘዘ።2. በሃይል መታ፥ ጠለዘ፥ ለጋ (ኳስን)። 3.(ዘይ.) መታ፥ ደበደበ።

**ጦዘጦዘ** ግ አረጀ፥ ሸመገለ።

**ጦዝጧዛ** ቅ ያረጀ፥ የሸመገለ።

***ጦዘጦዘ**

**ጦዝጧዛ** ቅ ከውካዋ።

**ተንጦዘጦዘ** ግ ተንከወከወ።

**አንጦዘጦዘ** ግ አንከወከወ።

**ጦዝጧዛ**[1] "**ጦዘጦዘ**" ስር ተመ.

**ጦዝጧዛ**[2] "***ጦዘጦዘ**" ስር ተመ.

**ጦጣ** ስ እንደ ዝንጀሮና ጉሬዛ ከዛፍ ላይ የሚወጣ፥ ብልጥ ነው የሚባል የዱር እንስሳ።(ስእሉን የዱር እንስሳት ስር ተመ.)

**ጦፈ** ግ 1. ነደደ፥ ተቃጠለ፥ ተንቀለቀለ (እሳት)። 2. (ዘይ.) በሃይል ተበሳጨ፥ ተናደደ። 3. ደመቀ፥ ተሟሟቀ። *ጨዋታው ጦፈ።*

**ጧፍ** ስ ለመብራት የሚያገለግል በሰም የተነከረ ክር ወይም ፈትል።

**ተጧጧፈ** ግ 1. ተቀጣጠለ፥ ተያያዘ (እሳት)። 2.ሞቀ፥ ደራ፥ ተጋጋለ።(ለምሳሌ ወሬ፥ ጦርነት፥...)።

**አጧጧፈ** ግ በሰፊው አካሄደ።*ንግዱን አጧጡፎታል።*

**ጧ**[1] የ "ጠ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

**ጧ**[2]

**ጧ ብሎ ተኝቷል** ሃይለኛ እንቅልፍ ወስዶታል።

**ጧ አለ** ግ 1. አንድ ነገር ሲበጠስ ወይም ሲፈነዳ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ። 2. ተበጠሰ። 3. ፈነዳ። 4.ኗ አለ፥ ተዘረረ፥ ተዘረጋ።

**ጧ ያለ ሜዳ** ስ ወጣ ገባ የሌለው ለጥ ያለ ሜዳ።

**ተንጧጧ** ግ ተንጣጣ፥ ተንጦሸጦሸ፥ ደጋግሞ ፈነዳ።

**አንጧጧ** ግ አንጣጣ፥ አንጦሸጦሸ፣ አፈነዳ።

**ጧሪ** "**ጦረ**" ስር ተመ.

**ጧት (ጠዋት፥ ጥዋት)** ስ ማለዳ፥ ንጋት ላይ ያለው ጊዜ።

**ጧፍ** "**ጦፈ**" ስር ተመ.